# የቀበና ማህደር

ከአገር ውጪ የሚኖሩ የቀበና አብሮ አደጎች ዓመታዊ መሰባሰቢያ ቀንን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ መጽሔት

ቁጥር 3 - ሐምሌ 2008 ዓ.ም ፡ ሲልቨር ስፕሪንግ ፣ ሜሪላንድ ፣ አሜሪካ ፡ www.yekebenasefer.com



ይህ ዕትም
ለውድ ወንድማችን
ለሰለሞን ሐድጉ ንጉሴ
(ጋንፋር)
መታሰቢያነት ይሆን
ዘንድ ተበርክቷል

# ከቀበና ማህደር

ከአገር ውጪ የሚኖሩ የቀበና አብሮ አደጎች ዓመታዊ መሰባሰቢያ ቀንን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ መጽሔት

ቁጥር 3 - ሐምሌ 2008 ዓ.ም | ሲልቨር ስፕሪንግ ፣ ሜሪላንድ ፣ አሜሪካ | www.yekebenasefer.com

## ማውጫ


የመጽሔቱ አዘጋጆች መልእክት ... ገፅ 2
አብሮ አደጎች ምን ይላሉ? ......... ገፅ 4
የልጆች አምድ ..................... ገፅ 12
እስቲ እናስታውሳቸው ............ ገፅ 14
ከዚህም ከዚያም.................... ገፅ 19
የቀበና ትዝታ ...................... ገፅ 22
የፎቶ ዓምድ ........................ ገፅ 26
ከግጥም አምባ...................... ገፅ 33



ዋና አዘጋጅ

ገዛኸኝ ታደሰ

የኢዲቶሪያል ኮሚቴ አባላት

ግርማ ታደሰ

ሰለሞን አስፋው

ዶ/ር ጌታቸው በላይነህ




ይህ ዕትም ለውድ ወንድማችን ለሰለሞን ሐድጉ ንጉሴ (ጋንፋር) መታሰቢያነት ይሆን ዘንድ ተበርክቷል

## ምስጋና

ለ2015ቱ የቀበና አብሮ አደጎች የመሰባሰብያ ቀን ዝግጅትና ለመጽሔቱም ማሳተሚያ ያግዝ ዘንድ፤ ከዛም አልፎ አንድነታቸውንና ትብብራቸውን ለመግለጽ ብሎም ለማረጋገጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቀቤዎች የገንዘብ አስተዋጽዖ አድርገዋል። የዚህ ስብስብ አስተባባሪዎችም ከልብ የመነጨ ምስጋናቸውን እያቀረቡ ይህ አይነቱ ድጋፍም እንደሚቀጥል ተስፋቸው ጽኑ ነው።

| | |
|---|---|
| ጌታቸው በላይነህ | 400.00 |
| ሰለሞን አስፋው | 400.00 |
| ወርቁ ደመና | 400.00 |
| ሙሉነህ ለገሠ | 400.00 |
| ሰለሞን ሐድጉ | 400.00 |
| ግርማ ታደሰ | 400.00 |
| አጥናፉ በቀለ | 400.00 |
| ጉቺ ሱራፌል | 400.00 |
| ገዛኸኝ ታደሰ | 400.00 |
| አልማዝ ሐድሩ | 200.00 |
| አሸናፊ ተፈራ | 60.00 |
| በለጠ ጌታቸው | 100.00 |
| አጅግአየሁ በፍቃዱ | 50.00 |
| እመቤት መኮንን | 50.00 |
| ኢትዮጵያ (እናና) አለማየሁ | 50.00 |
| ፈለቀች እሸቴ | 100.00 |
| ለገሠ ዘውዴ | 200.00 |
| መለሰ ተፈራ | 100.00 |
| መሠረት፣ ሂሩት፣ ስምረትና ኃረገወይን በቀለ | 200.00 |
| ታደሱ ገ/ማርያም | 100.00 |
| ቴዎድሮስ (ቴዲ) እሸቴ | 50.00 |
| ተረፈ ተስፋዬ | 100.00 |
| ትዝታ ሚደቅሳ | 50.00 |
| ፀሐይ ኃይሉ | 50.00 |
| ይትባረክ ጀምበሬ | 200.00 |
| ጠቅላላ ድምር | $5,260.00 |


KWIK Design & Printing
www.kwikdp.com • 619-206-0921 (Assaye)
Printed in U.S.A

# የመጽሔቱ አዘጋጆች መልእክት



ቁጥር 2 መጽሔት ሲታደል

የሰማይ እርቀቱን፣ የኮከብ ብዛቱን፣ የፀሐይ ድምቀቷን፣ የውቅያኖስ ጥልቀቱን ያህል የምትናፍቁን ቀበኖች፤ እንደምን ከርማችኋል? እንደምንስ ሰንብታችኋል? እነሆ በቁጥር 2 "ከቀበና ማህደር" እትም አማካኝነት ሰላምታ ከተለዋወጥን ድፍን አንድ ዓመት ሆነን። ቢቻል በየዓመቱ፤ ካልሆነም በየሁለት ዓመቱ ይህችን ተናፋቂ መጽሔት ይዘን ብቅ እንላለን ብለን ቃል በገባነው መሠረት እነሆ ቁጥር 3 "ከቀበና ማህደር"ን ለንባብ አብቅተናል። በቁጥር 2 እትም ላይ እንደገለጽነውና እንዳሳሰብነው፣ ይህች መጽሔት የሁሉም የቀበኖችና ቀበናን የሚሉ ወገኖች ንብረት ናት። የቀጣይነቷ እጣ ፋንታም በነዚሁ በቀበኖች ትከሻ ላይ ነው የሚወድቀው። ይህን ጥሪ በማክበርም በርካታ ቀበኖች ብዕራቸውን አንስተዋል። "ቀበናን ያላችሁ፣ እስቲ እንያችሁ" ለሚለው ጥያቄም መልስ ሰጥተዋል። ውብ፣ ወብ ጽሁፎችንና ግባቶችን ጀባ ብለውናል። ሰለሆነም እነሆ ቁጥር 3 ዕውን ሆናለች። የሁላችንም ብዕር እንዲህ ከተባ፤ ሁላችንም ያቅማችንን ከሰነዘርን፣ ይህች መጽሔት እድሜ ይኖራታል፤ ለትውልድም ትተላለፋለች።

የቁጥር 3 "ከቀበና ማህደር" ቅርጽ እንደ ቀደሙት መጽሔቶች (ቁጥር 1 እና ቁጥር 2) ቢሆንም ይዘቱ ግን ሙሉ በሙሉ ያተኮረው በዚያችው በመንደራችን ዙርያ ነው። ብዙ አንባብያንን የሚያስደምሙ የቀበና ታሪኮች ቀርበዋል። የውድ ወንድማችን የጋንፋሬም አጭር የህይወት ታሪክ ተካቷል። የቀበና ልጆች ብዕር ጉልበትም ታይቷል። ይሄ ገና የመጀመርያው ነው። ወደፊት ደግሞ ከላይ በቀረበው መሠረተ "ቀበናን ያላችሁ፣ እስቲ እንያችሁ" ለሚለው ጥሪ ምላሽ እንደሚጎርፍ ጥርጥር የለንም። ጽሁፎች ወረፋ የሚጠብቁበት ጊዜም እሩቅ አይሆንም።

በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የሶስተኛ ዓመቱ የቀበና አብሮ አደጎች የመሰባሰብያ በዓል እጅግ ደማቅ በሆነና ልዩ ውበትን በተላበሰ ስነስርዓት ጁላይ 4 ቀን 2015 ዓ/ም በሰሜን አሜሪካ፣ ሜሪላድ ግዛት፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ከተማ በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ ውሏል። ይህ ዝግጅት በእውነቱ ከበፊቶቹ ሁለት ዝግጅቶች በብዙ ነገሮች የተለየ ነበር። በዓሉ የተከበረበት ስፍራ እጅግ ውብና ምቹ ነበረ። በስፍራው የተገኙትም የቀበኖች ቁጥርም በርካታ ነበር። ከህፃናት እስከ አዛውንት ሁሉም ቀበኔ ነበር የታደመው።የውዷ እናታችን የወ/ሮ ማሚቴ ዳኜ በመሃከላችን መገኘትም ለበዓሉ ትልቅ ውበት፣ ግርማ ሞገስና ድምቀት አላብሶታል። የበዓሉ ዝግጅትና ቅንብር፣ የቀረበው ምግብና መጠጥ፣ መስተንግዶው፣ እንደው በአጠቃላይ እንከን የማይወጣለት ልዩ በዓል ነበር። በተጨማሪም፣ ብዙ ታዋቂ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን ካፈራችው ቀበና የተገኙት የአብራክ ልጆቿ ለመጀመርያ ጊዜ ትጥቃቸውን አሳምረው በሜሪላንድ ምድር ላይ የጥንት የእግር ኳስ ችሎታቸውን የፈታተሹበት ዝግጅት ነበር።

ቢሻን ቀበና ደመቅ ሞቅ ብሎ እየተጫወተና አዳራሹን በሞላበት ቅጽበትም የዘፈኑ ባለቤትና  ብርቅየው የቀበና ፍሬ ድምጻዊ ፀሐዬ ዮሐንስም ማንም ሳይገምትና ሳይጠረጥር ወደአዳራሹ ዘለቀ። ቤቱም በእልልታ፣ በጩኸትና ፉጨት ደመቀ። ሁሉም ከመቀመጫው ተነስቶ እንኳን ደህና መጣህ አለው። ቢሻን ቀበናንም እያንጎራጎረ በውዝዋዜ አጀበው። ከዚያም፣ ቃላት ሊገልጹት በማይችሉትና ልብን በሚነካ ሁኔታ ሁሉም በየጠረጴዛው ዙርያ አፍ ለአፍ ገጥሞ የቀድሞ ትዝታውን እያወጋ፤ ያለፈውን ደስታም ሆነ ሃዘን እየዳሰሰ ለዘመናት ተያይቶ የማይተዋወቅ ሁሉ ጥግ ጥጉን ይዞ ወጉን ሲኮመኩም አመሸ። አንዳንዴም እየተሳሳቀ፣ መለስ ብሎም በእንባ ፊቱን እያበሰ አንዱን ሲጥል፣ ሌላውን ደግሞ ሲያነሳ ቆየ። ሁሉም ታዳሚ እያንዳንዷን ደቂቃ በስስትና በጥንቃቄ ነበር የሚጠቀምባት። አይችልም እንጂ ቢችልማ ሰዓቱን ቀጥ አድርጎ፣ ደቂቃና ሰኮንዱን አሉበት ላይ አቆይቶ ይህን መቼም የማይገኘውን ወግና ጨዋታ ዝም ብሎ፣ ሲኮመኩም መክረምን በመረጠ ነበር።በፊልምና በፎቶግራፍ የተደገፉ በቀበና ዙርያ የተቀነባበሩ ታሪኮችም ለእይታ በቁ።

በስተመጨረሻም ጸጥ እረጭ ብሎ፣ ወግና ስርዓቱን ጠብቆ፣ በቁም ነገር እየተደማመጠ ስለ አብሮ አደጎቹ ስብስብ የሚለውን

# የመጽሔቱ አዘጋጆች መልዕክት

አለ። መከረ፤ ተወያየ፤ የስብስቡን ዋና ዓላማ ሳይስት አሁን እያከናወነ ካለው ተግባር አለፍ ብሎ ምን ማድረግ እንደሚችል ወይም ምን ማድረግ እንደሚገባው ተነጋገረ። ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰነዘሩ አዳዲስ ሃሳቦችንም አስተናገደ። በተነሱት ሃሳቦች ላይ ሁሉ ስምምነት አደረገ ወይም የጋራ ግንዛቤ አገኘ። ለመጪው ዓመትም በህይወት መድረሱን ተስፋ በማድረግ እቅድ ነደፈ። በመቀጠልም ቁጥር 2 "ከቀበና ማህደር" እትምም ለታዳሚው ተሰራጨ።

የቀበና ሰው በስነስርዓቱ መደምደሚያ ላይ የከርሞ ሰው ይበለን፣ በሰላም በጤና ጠብቆ ድጋሚ ለመገናኘት ያብቃን እየተባባለ፣ አንገት ለአንገት እየተቃቀፈ መሰነባበቱን ተያያዘው። አዎ፤ እንደው የአፍ ልማድ ስለሆነና፣ ወግ ለማድረስ ብለን አይደለም "...በሰላምና በጤና ጠብቆ ድጋሚ ለመገናኘት ያብቃን..." የምንባባለው። ከመካከላችን ማን ተረኛ እንደሆነ ስለማናውቀው ነው። እንዲያ ቢሆንማ እኮ፤ ተረኛው ቢታወቅማ ኖሮ ለዚህ ስብስብ ህልውና ይሚገት የነበረው፣ ለጥንስሱም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው፣ በዚህ ምሽት በዓል ላይም ሆነ ላለፉት ሦስት ዓመታት በጥንቃቄ ስብስቡን ሲመራ የነበረውና ከባድ ህመም አሸንፎ በድል ብቅ ያለው የቀበናና የስብስባችን አድባር የነበረው ጋንፉር ከጥቂት ወራት በኋላ እንደሚለየን፣ በቀጣይ በዓሎቻችን እንደማይገኝ ብናውቅ ኖሮ ስንብብታችን ሌላ መልክ ይኖረው ነበር።

አዎ፤ የቀበና ብርቅዬ ልጅ፣ የቀበና አድባር፣ ሁለ ገቡ፣ የሰው መውደድ ሃብቱ ንብረቱ የሆነው ጋንፉሬ ጭራሽ ባልተጠበቀ ሁኔታ ላንዴና ለሁሌም ውድ ቤተሰቡንና ቀበኖችን ተሰናብቷል። አዎ፣ የጋንፉሬ እረፍት የሁሉንም ልብ ነክቷል። ሞት ለማንም የማይቀር የፍጥረታት ሁሉ ዕጣ ፋንታ ነው። ነገር ግን ከወጣትነቱ ዕድሜ አንስቶ ከብዙ አደጋና ፈተና፣ እንዲሁም ከከፋ የጤና ችግር አምልጦ፣ በወቅቱ እነበረበት የህይወት ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው እንዲህ ባጭር ሲቀጭ ያስደነግጣል፣ ከልብ ያሳዝናል።

ጋንፉር ከልጅነቱ ጀምሮ ባደገበት ሠፈሩ ቀበና እና በአካባቢው በሰው ወዳድነቱ፣ ሰብዓዊ ምግባሩ፣ አስተባባሪነቱና ሁለገብ የሕዝብ አገልግሎቱ የታወቀ ወጣት ነበር። በተለያዩ ድርጅቶችና ማኅበራት ውስጥ በንቃትና በትጋት በመሳተፍ አብሮ የመኖርን፣ የማኅሕበራዊ ግንኙነቶችንና የሕዝብ ፍቅሩን ጥልቀትም በተግባር አስመስክሯል። ከሀገሩም ወጥቶ በስደት በኖረባቸው ጊዜያት ሁሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከተዋወቃቸው ሰዎች ጋራ በመሆን መረዳጃዎችንና ማኅበራትን ለመመስረት ሐሳቦችን ያመነጭና ያንሸራሽር ነበር። ተሳክቶለትም የመሰረታቸው ማኅበራትም አገልግሎት እያበረከቱ ይገኛሉ።

በስደት ኑሮ ውስጥ ሳለም ሁሌም ቀበና ሰፈሩን እንዳሰበና እንደናፈቀ ነበር የኖረው። የቀበና አብሮአደጎቹንም ለማሰባሰብ ያላሰለሰ ጥረት ያደርግ ነበር። ይህ ህልሙም ለረዥም ጊዜ ሳይሳካለት ቆይቶ ነበር። ከሰባት ዓመት በፊት ጋንፉርና ሶስት የቀበና አብሮ አደጎቹ በአርሊንግተን፣ ቨርጂኒያ ፔንታገን ሞል ውስጥ በሚገኝ የስታር ባክስ ውስጥ ተቀምጠው ሳለ እሱ ባመነጨው የአብሮ አደጎች መሰባሰብ ሀሳብ ላይ ብዙ ተወያይተው ነበር። የጋንፉር ሀሳብ ያደላ የነበረው ተሰባስቦ ማኅበር በመመስረትና በሃገር ቤት የሚገኘውን ያሳደገንን የአካባቢያችንን ሕዝብ እንርዳ የሚል ነበር። ይህ የተቀደሰ ሃሳብ ግን በወቅቱ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል።

በኋላም እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ2013 ዓ/ም መጀመሪያ ላይ ከቀበና አብሮ አደጎቹ የቀረበውን የመሰባሰብ ጥያቄ "የተቀደሰ ሀሳብ ነው" ብሎ በመቀበል ለስኬታማነቱ ያላሰለሰና ያልተቋረጠ ጥረት አድርጓል። ከ35 ዓመታት በላይ ተለያይተን የነበርነው አብሮ አደጎቹ የመጀመሪያውን ስብሰባችንን እንድናደርግም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። የዝግጅቱ መሪ በመሆንም ለረጅም ዓመታት ተለይቷቸው ከነበሩት ብዙ የቀበና አብሮ አደጎቹ ጋራ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፭ ዓ/ም (July 6th, 2013) በሲልቨር ስፕሪንግ፣ ሜሪላድ ተገናኝቶ ናፍቆቱን ተወጥቷል። ምንም እንኳን ስኬታማ ባይሆንም፣ በሃገር ቤት ያለውን ያሳደገንን የአካባቢያችንን የሕዝብ ዕድር እንርዳ የሚል ሀሳብ እንደገና በዚህ በአዲሱ የአብሮ አደጎቹ ስብሰባዎች ላይ በተደጋጋሚ አቅርቦ ነበር።

ለሁለተኛው ዓመት ግንኙነት ዝግጅት ደፋ ቀና እያልን ሳለ፣ በጋንፉር ላይ አስደንጋጭ የሆነ የጤና መታወክ ደረሰበት። ሁኔታውም በመሀከላችን ድንጋጤን ፈጠረ። ጋንፉርም በህክምና ሲረዳ ቆይቶ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ከዛ መጥፎ በሽታ ዳነ። የኛም ደስታ እጥፍ ድርብ ሆነ። ይህንን የምሥራችም ይዘን የሁለተኛውን የቀበኖች መሰባሰብያ ዓመታዊ በዓል ፍጹም ሊረሳ በማይችል ታሪካዊ ሁኔታ አከበርን። የከርሞ ሰው ይበለን ተባብለንም ተለያየን። በመቀጠልም የሦስተኛውን ዓመት ግንኙነት (በዓል) ዝግጅት ተያያዝነው። ጋንፉሬም ከባልንጀሮቹ፣ ከአብሮአደጎቹ ጋር በትጋት መስራቱን ቀጠለ። ውጤቱም አማረና የሦስተኛውን የቤተሰብ፣ የቀቤዎች መሰባሰብያ ዕለትንም እጅግ ልዩና ደማቅ በሆነ ሁኔታ አከበርነው። ጋንፉሬም መቼም ሊረሳ በማይችል ለዛና ቅንብር የበዓሉን ስነስርዓት መራ።

አለመታደል ሆነና፤ የዘንድሮውን (የአራተኛ ዓመት) በዓላችንን ለማክበር በዝግጅት ላይ እያለን ባላሰብነውና ባልጠበቅነው ሁኔታ ወንድማችን፣ ጉዳችንና አድባራችን የነበረው ጋንፉር ከዚህ አለም በሞት ተለየን። መራራ ሃዘንም ጣለብን። የሚገርመው፣ ለዚሁ በዓል ዝግጅት የተደረገውን የህዳር ፳ ቀን ፳፻፰ ዓ/ም (November 29th, 2015) ስብሰባ ጋንፉር የመራው እጅግ በሚያስደንቅና ጭራሽ ሊረሳ በማይችል ሁኔታ ነበር።

ጋንፉር ወደኋላ ቀርተን ወረፋ በመጠባበቅ ላይ ላለነው ወገኖቹ ብዙ የቤት ሥራና አደራ ሰጥቶ ነው ያለፈው። ከነኚህም ዋና ዋናዎቹ፤ ሃገራችንን መውደድ፣ ለጥሪዋም ምላሽ መስጠት፣ እርስ በርሳችን መዋደድና መከባበር እንዲሁም ላሳደገንና ለዚህ ላበቃን ወገናችንና ሠፈራችን የሚቻለንን ማድረግ።

በዚህ በቁጥር 3 እትም ላይ የጋንፉሬን የሕይወት ታሪክ አቅም በፈቀደ ሁሉ ለማቀነባበርና ለማቅረብ ተሞክሯል። ይህ እትምም ለዚህ ውድ የቀበና ልጅ መታሰብያነት ውሏል።

# አብሮ አደጎች ምን ይላሉ?



ከሀገራችን ከኢትዮጵያ ውጪ የምንኖር የቀበና ኮሪያ ሠፈር አብሮ አደጎች በዓመት አንዴ መገናኘት ከጀመርን እነሆ ዘንድሮ አራተኛ አመታችን ሆነ። እስቲ ያለፈውን ዓመት ስብሰባችንን ቃኘት እናድርግና ወደ ዋናው ጉዳያችን እንመለስ።

ያለፈውን የጁላይ 4 ቀን, 2015 ዓ/ም ስብስባችንን ቀደም ካሉት ሁለት አመታት ለየት የሚያደርጉት አንዳንድ ነገሮች ተስተውለዋል። እነሱም አንደኛ የተዘጋጀበት ቦታና አዳራሹ ሲሆን ብዙዎቻችንንም እንዳስደሰተ እሙን ነው። የቦታው አቀማመጥ፣ የአዳራሹ ስፋትና የማዕድ ቤቱ አመቺነት፤ የወደፊቱን ስብሰባዎቻችንንም የምናካሂድበት እንዲሆን መርጠነዋል።

ሁለተኛ የቀበና ኮርያ ሰፈሯ ታላቋ እናታችን ወሮ ማሚቴ ዳኜ በዛን እለት ከልጆቻቸው ጋር በመሆን በመካከላችን በመገኘት ምሽቱን ማሳለፋቸው ነበር። የእኚህ ታላቅ እናት በመካከላችን መገኘት በእውነቱ ታላቅ ክብርንና ደስታን ሰጥቶናል። እድሜያቸውን አርዝሞ አይናቸውን እንድናይና አብረውን እንዲሆኑ የፈቀደውን፣ እግዚአብሔርን፣ እያመሰገንን፤ በሚቀጥሉት ዝግጅቶቻችንም አብረውን እንደሚያሳልፉ ተስፋችን ከፍ ያለ ነው። ለሌሎች እናት አባቶቻችንም ወደ ዝግጅታችን እንዲመጡ መልካም ምሳሌ ሆነውልናል። እግዚአብሔር ያክብርልን እንላለን።

ሦስተኛውና ጎላ ብሎ የታየውና እሰየው የሚያሰኘው ደግሞ፤ ቀደም ባሉት ሁለቱ ተከታታይ ስብሰባዎቻችን ላይ ያልተገኙ በርካታ የቀቤ ተወላጆች፣ ነዋሪዎችና አብሮአደጎች የመካፈላቸው ጉዳይ ይሆናል። አብረን ማደጋችንና የምንጋራቸው ትዝታዎቻችን የመሰባሰባችን ዋልታ እንደመሆናቸው ሁሉ፤ አስደሳችነታቸውና ማራኪነታቸው የጋራችን ይሆናሉ ማለት ነው።

አራተኛው ደግሞ የቢሻን ቀበና ባለቤትና የኛው፣ የቀበናው፣ የኮርያ ሰፈሩ ብርቅዬ ልጅ ፀሐዬ ዮሐንስ ሳይታሰብና ሳይጠረጠር ከተፍ ማለቱ ነበር። የፀሐዬ በዚህ ቦታ ላይ መገኘት ለበዓሉ ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል። ፀሐዬ፣ ምስጋናችን ይድረስህ። በየዓመቱም አብረኸን በመሆን ይህን በዓል (ስብስብ) እንዲሁ በድምቀት እናከብራለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

አምስተኛው ደግሞ ለመጀመርያ ጊዜ የተካሄደው የእግርኳስ ጨዋታ ነበር። የጥንቶቹ የጃንሜዳ፣ የኖራ ሜዳና የሐኪም ሜዳ የኳስ ጥበበኞች አቅማቸውን በመጠኑም ቢሆን ፈታትሸዋል።

በያለንበት ሆነን መተሳሰባችንና መነፋፈቃችን አልቀረም። ግና ተገናኝተን ማውጋቱ፣ በትዝታ አብሮ መንጎዱ ምንኛ አስደሳች እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ታዲያ ወደስብሰባችን ላልመጣችሁ ሁሉ የምንላችሁ ቢኖር፤ የሚቻላችሁን ሁሉ ጥረት አድርጋችሁ፤ እባካችሁ በዓመት አንዴ እንኳን እንያችሁ። ሌላው የምንጠይቃችሁ፤ በዚህች በዓመት ወይም በሁለት ዓመት አንዴ በምትታተመውና በምትወጣው መጽሔታችን የምትችሉትን ያህል ተሳትፎ እንድታደርጉ ነው።

ይህንንም መሠረት በማድረግ፣ በዚህ ዓመት መጽሔታችን፤ አብሮ አደጎች ምን ይላሉ በሚለው አርእስት ስር የተለያዩ የቀቤ ልጆች የሚሉን አላቸውና እስቲ እናድምጣቸው።

## የቀበና 06 አብሮ አደጎች መሰባሰብ ከበስተጀርባው ያለው ሚስጥር ምን ይሆን?

ከእለታት አንድ ቀን ጠዋት አረፋፈዱ ላይ ወደ ሥራ ልሄድ እየተጣደፍኩ እያለሁ፤ የባለቤቴ ወንድም የሆነው አቶ አጥናፉ በቀለ ስልክ ደውሎ ትንሽ ሠላምታ ቢጤ ከተለዋወጥን በኋላ "ስማ የቀበና 06 አብሮ አደጎች ዓመታዊ በዓል እየደረሰ ስለሆነ፥ እባክህን ትንሽ ጽሁፍ ብጤ ብትጽፍ ብዬ ነው የደወልኩልህ" ይለኛል። እኔም ቸኩዬ ስለነበር በደመነፍስ ዝም ብዬ "...ሳላስብበት እሺ.." ብየው ተለያየን።

*መሥሪያ* ቤቴ እስከምደርስ ድረስ በመንገዴ ላይ ምን እንደምጽፍ ግራ ገብቶኝ ሳሰላስል በዓዕምሮዬ ውስጥ በድንገት ይህ በአርእስቱ ላይ የምታነቡት ጽሁፍ "የቀበና 06 አብሮ አደጎች መሰባሰብ ከበስተጀርባው ያለው ሚስጥር ምን ይሆን?" የሚለው ሃሳብ ድቅን አለብኝ። ነገር ግን፣ የሥነ ጽሁፍ ብቃትና ልምድ ስላልነበረኝ ጭንቀት ያዘኝ። ደግሞም ለዚህ ለቀበና የ06 ቀበሌ የአብሮ አደጎች ስብስብ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ እምነት አደረብኝ። ስለዚህ፣ ለጊዜው የመጣልኝ ሃሳብ ይህ ብቻ ስለነበረና አርእስቱን ብቻ በእጅ ስልኬ ላይ ማስታወሻ ጽፌ ወደ ሥራዬ ገባሁ። አዎን፤ ሚስጥሩ ምንድን ነው? እነዚህ አብሮ አደጎች እስከዛሬ ድረስ እንደዚህ ጠንካራ የወንድማማችነትና የእህትማማችነት፤ የአብሮነት፤ የቤተሰባዊነት ፍቅር ተላብሰው የኖሩት ሚስጥራቸው ምን ይሆን?

እንደምታውቁት እኔ በቀበና ሠፈር ተወልጄ ያላደግሁ ሰው ብሆንም፤ እንደማንኛውም ነዋሪ ተከራይቼ ከመቆየት ብዛት ከዚያው ካለሁበት ጎረቤት በጣም ከሚታወቁት የሠፈር አዛውንቶች መካከል የ፶ አለቃ አንገናፍር ደምሴን ልጅ አግብቼ ሦስት ሴቶችና አንድ ወንድ ልጅ ወልጄ ያሳደኩበት ሠፈር ስለሆነ ለጽሁፌ መነሻ ጥንካሬና ብርታት ሰጥቶኛል። የቀበሌው ነዋሪ ስለሆንኩም፤ የቀበሌ የዜግነት ግዴታዬን መወጣት ያለብኝ መሰለኝ። ይህን በማድረጌ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል።

በአጠቃላይ፤ በቀበና 06 ቀበሌ እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ከ 1957 - 1993 ዓ/ም ድረስ ከ 36 ዓመታት በላይ ኖሬበታለሁ። በዚህ ረዥም ጊዜ፤ ከአዋቂውም፣ ከልጁም፣ ከትልቁም፣ ከትንሹም ከጎረቤቶቼም ይሁን ከዕድርተኞቼ ከአቡነ ገ/መ/ቅዱስ ዕድር፣ ወይም ከአጥቢያ ኮከብ ዕድር ይህ ቀረሽ የማይባል ፍቅርና አክብሮት ሲቸረኝ ቆይቻለሁ። በዚህ አጋጣሚ ሁሉም በያሉበት ምስጋናዬ ይድረሳቸው፤ አመሰግናለሁ፤ እወዳችኋለሁ። ታዲያ እኔን እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ የሚገርመኝ፤ ይህንን ህብረተሰብ እንደብረት ምሰሶ እንደዚህ አጠንክሮና አስተሣሥሮ ያቆየው ምን ስለሆነ ነው? ምን አግኝቶ ነው?

ስለቀበና ህብረተሰብ ፍቅር እንደዚህ በቀላሉ ተወርቶ መች ያልቃል። ጎረቤት ታመመ ሲባል መጠያየቁ፣ እከሌ ሞተ ሲባል እሮጦ ሄዶ ለቅሶ መድረሱ፣ አስከሬን ተሸክሞ ሄዶ ቤተ ክርስቲያን መቅበሩ፣ ከዚያ መልስ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ተቀምጦ ማስተዛዘኑ፣ አይደለም ሰው እንስሳው ውሻዬ ቦቸራ እንኳን ሳይቀር ቤተ/ክ ድረስ ሄዶ ቀብሮ መጥቶ ተመልሶ ድንኳን አጠገብ ሦስት ቀን ሙሉ በመገኘት ቀን ቀን ሰው በመቀበል፣ ማታ ማታ ደግሞ የድንኳን ጥበቃ በማከናወን ሥራ የሚሠራው ከምን የመጣ መለኮታዊ ተዓምር ነው? እውነተኛ ፍቅር! ከልብ የመነጨ ፍቅር! የቀበና ፍቅር አይጠገቤ!

አንድ የሰፈር ነዋሪ ገና ከቤቱ ደጃፍ እንደወጣ የሚገጥመው ሞቅ ደመቅ ያለ የእጅ መጨባበጥ፤ መተቃቀፍ፤ መሳሳም አያድርስ ነው፤ ንፁህ ፍቅር። እንደዚህ ሃገር ሰዎች "HI BUDDY, WHAT'S UP?" ብሎ ነገር የለም። አርተፊሺያል ፍቅር አናውቅም፤ አለመደብንም። እምዬ የቀበና ፍቅር። ወደ ላይ ወደ እንጦጦ ወረዳ ፍ/ቤት (ድድ ማስጫ) አካባቢ ሲወጣማ ያለው ጨዋታና ሁካታ አሸንቡሬሬ ነው። አስር ሳንቲም ወይም ሃያ ሳንቲም ለማግኘት ሲሉ የጫማ ጠራጊ ሊስትሮዎች የሚያሳዩት እሽቅድምድሞሽ አስቂኝ ድራማ ነው። እዚያው ሳሉ በነፋሻ አየር ውስጥ ሾልኮ ከአፍንጫ የሚደርሠው ያካባቢው የጠጅና የተመሰገን ሥጋ ቤት ጥብስ ነፍስ ነው፤ አይጣል ነው። ይህ ሁሉ የቀበና ትዝታችን ነው፤ እንዴት ይረሣል። ወገኖቼ፣ አሁን ንገሩኛ፤ ምንድን ነው ሚስጢሩ ታዲያ? አይደለም ቀሪው ቀበና ያለው ህዝብ፤ በየውጭ ሃገራት የሚኖረው የቀበሌው ተወላጅ በስደት ዓለም እየኖረ እንኳን ይህንን አንድነት አፅንቶ ለማኖር ምን አስገዳጅ ሁኔታ ገጠመው? እኔ እስከማውቀው ቀበና 06 ቀበሌ የፍቅር አምባ፤ ለሌላው ሁሉ ተምሳሌት የሚሆን ሕዝብ ነው። መከባበር፣ መቻቻል፣ መጋባት፣ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣትን የሚወድ። አማራ፤ ኦሮሞ፤ ጉራጌ፤ ትግሬ፤ ሶማሌ እና ሌሎችም ብሄር ብሄረሰቦች ተዋደውና ተከባብረው ለዘመናት የኖሩበት በፍጹም ኢትዮጵያዊነት ላይ የተመሠረተ የአንድነት ተምሳሌት የሆነ ሠፈር ነው።

የቀበና ነገር ገና ብዙ ብዙ መጠናት ያለበት ይመስለኛል፤ ደግሞም ነውም። የጂኦግራፊያዊ አቀማመጡ አንዱ ክፍል ነው። ቆላማ፣ ደጋማና ወይና ደጋማ የቦታ ቅርፅ ያለው። ዋናው መኩሪያችን፣ መጠሪያችን፣ መከበሪያችን የሆነው "የእኛ የግላችን" የምንለው የቀበና ወንዝ ለኛ የአባይ ወንዛችን ያህል ነው። ዱቤ ባህር ለኛ የጣና ሃይቃችን ያህል ነው። በአንድ ወቅት የቅርብ ጓደኛዬ የሆነ በዕድር ስብሰባ ላይ እንዲህ ብሎ ነበር "የቀበና ሕዝብ ኑሮው ከድህነት በታች ቢሆንም፤ የዕውቀት ባለፀጋ ነው" ብሎ ነበር። ይህንን አባባል እኔም እጋራለሁ፤ ትክክለኛ አባባል ነው። አዎን፤ በአሁኑ ወቅት ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን እየደረሱና እግር በእግር እየተኩን ነው።ዶክተሮች፣ መሃንዲሶች፣ አውሮፕላን አብራሪዎች፣ ፕሮፌሰሮችና ሌሎችንም ባለሙያዎች እያፈራች ያለች ቀበሌ ነች። ስለዚህ ማን ያውቃል አንድ ቀን፤ ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ተዓምር የሆነ ሥራ ሠርተው ዓለምን ጉድ ያስብሉ ይሆናል።

ለምሳሌ፤ ጃንሜዳን (ይህ ቦታ የቀበና ክልል መሆኑ እንዳይዘነጋ) በዓለም ታዋቂ ከሆኑት ከተሞች እንደ ማንሀተን (ኒውዮርክ)፣ ቡርጅ ካሊፋ (ዱባይ) እና ሲንጋፑር ከተሞች ሰማይ ጠቀስ የሆኑ ሕንፃዎች ሊያጥለቀልቁት ይችላሉ። ዱቤ ባህርም ተገድቦ ትልቅ የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ ይሆንና ለአካባቢው ቀበሌዎችና ከተሞች መብራት የምንሸጥበት ጊዜው እሩቅ አይሆንም የሚል ከፍተኛ እምነት አለኝ። ይህ የጊዜ ጉዳይ እንጂ፤ የማይቻል ነገር

# አብሮ አደጎች ምን ይላሉ?

የሚቻልበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው። ይቻላል!!!

እንደሚባለው ከሆነ፡ ቀደም ሲል በነበረው የሕዝብ ቆጠራ፡ የቀበና 06 ቀበሌ የሕዝብ ብዛት ከ 13,000 ሺህ - 15,000 ሺህ ይገመታል። የዚህ ሁሉ ሕብረተሰብ የፍቅር ትስስር ሊመሠረት የቻለው፤ ቀደምት ቤተሠቦቻችን አብዛኛዎቹ ወታደሮች ስለነበሩ፤ ከኮሪያና ከኮንጎ ዘመቻ መልስ ባጠራቀሟት ገንዘብና የደም ካሳ በጭሠኝነት በህብረት ቦታ እየገዙ፣ እየተመሩና እየተከራዩ ትዳር መሥርተው ልጅ ወልደው የቆዩ በመሆናቸውና፤ በየጦር ግንባሩ አብረው ሲሞቱ አብረው ሲቆስሉ ሲደጋገፉ ሲተዛዘኑ አብረው ሲራቡና አብረው ሲጠሙ የነበሩ፤ በመከራና በችግር ጊዜ የተፈተኑ የልብ ፍቅረኛሞችና እንደ ወንድማማችና እህትማማች ሆነው ለብዙ ጊዜ በፅናት በመቆየታቸው እንደሆነ አያጠራጥርም። ይህ ጦር በውጊያ ብቃቱ አንቱ የተባለ ጠንካራ እና በዲሲፕሊን የታነፀ ሠራዊት እንደነበርና፤ ለዚህም ብቃትና ችሎታው ከተባበሩት መንግሥታት ተሸላሚ እንደነበረ ታሪክ ይመሠክራል።

ይህ ጦር ለአንድ ዓላማ የቆመ አንድ እናት ሃገር ወይም ሞት ብሎ ግንባሩን ለጥይት ደረቱን ለሳንጃ በመስጠት ከጠላት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቆ የተዋደቀ ሲሆን፤ የጦሩ ባልደረቦችም ጀግኖቹ አባቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ነበሩ። እንደዚህ በወሬ ስናወራው ቀላል ነገር ይመስላል፤ በግዳጅ ላይ ሆኖ ሲያዩት እንዴት ከሬት በላይ መራራና ዘግናኝ እንደሚሆን መገመት አይሳንም። "ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ" እንደሚባለው፤ የተፃፈ ታሪክ ማንበብ ብቻ ሣይሆን፤ አሁንም በህይወት ያሉ ቤተሰብና ጎረቤቶቻችን ያሉ ስለሆነ ከነሱ መስማት ይቻላል።

ጎበዝ፤ በህይወትና በሞት መካከል የተፈተነ ፍቅር፤ እውነተኛ ፍቅር፤ ለወንድማቸው ሲሉ ህይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ጀግኖች አባቶች ነው ያሉንና የነበሩን። ለወገንና ለሃገር አንድነት ሲሉ ክቡር ህይወታቸውን የሰጡ አንበሶች፤ የምናፍርባቸው አባቶች ሣይሆኑ የምንኮራባቸው፤ መተኪያ የሌላትን አንድን ህይወት መሥጠት ማለት ምን ማለት ነው? መልስ ስጡኛ! ሚስጥሩ ምንድን ነው? ለኔ እንቆቅልሽ ሆኖብኛል። መልስ ከእናንተ እፈልጋለሁ፤ እጠብቃለሁ? ህይወትን የሚያክል ነገር በፍቅር የመቀየር ጨዋታ ለማን፤ ለምን ሲባል? ይህ የቀደምት ቤተሰቦቻችን በአብሮነት ተሠባስቦ በፍቅር የመኖር ልምድ ለዚህ ለአሁኑ ለቀበና 06 ቀበሌ አብሮ አደጎች ወንድማማችነትና እህትማማችነት ፈር የቀደደ እንደሆነ አያጠራጥርም። ይህ አፈታሪክ ሣይሆን ብዙዎቻችን በህይወት ያለን ስለሆነ ህያው ምስክሮች ነን።

ስለዚህ እናንተ የቀበና 06 ቀበሌ አብሮ አደጎች ለዚህ ለወንድማማችነትና እህትማማችነት ህብረታችሁ እስቲ ዋናው ምክንያታችሁና ሚስጥራችሁ ምንድን ነው? መጀመሪያ ለሴቶቹ ጥያቄ፤ የገመድ ዝላዩ ነው? የሠኞ ማክሠኞ ጨዋታው ነው? ኩኩሉ አልነጋም ሌሊቱ ነው? የአበባየሆሹ ዘፈን ነው? ንገሩና ትውስታችሁን አድራጎታችሁን?

ወንዶቹስ ብትሆኑ፤ የብይ ጨዋታው ነው? ወይንስ በጃንሜዳ፣ በሽክላ ሜዳ፣ በኖራ ሜዳና በሐኪም ሜዳ የእግር ኳስ ጨዋታው? ወይንስ የቀበና ወንዝ የዱቤ ባህሩ ዋና? ወይንስ የአልጋ ወራሽ ጫካ የችቦ እንጨት ለቀማው? ወይስ ደግሞ የቡሄ ጭፈራው?

ንገሩና ምንድን ነው ሚስጥራችሁ እንደዚህ በፍቅር ያስተሳሰራችሁ? በሚያስቀና መልኩ የትም ተሄደ የት፤ አውስትራሊያ በሉት፤ ደቡብ አፍሪቃ በሉት፤ በአውሮፓ አህጉራት በሉት፤ በካናዳ ወይም በአሜሪካ የሚፈላለገው በኢትዮጵያዊነቱና በአንድነቱ የሚያምነውና የሚኮራው ይሄው የፈረደበት የቀበና 06 ወጣት ብቻ ነው። ይህን የዓላማ ፅናትና ትሥሥር ያመጣው ጀግኖቹ አባቶቻችሁ የዘሩት የፍቅር ፍሬ ሣይሆን ይቀራል? ንገሩና የናንተን መልስ ዛሬ እንስማ? ትዝታችሁን አምጡትና ሚስጥራችሁን ንገሩን። አትደብቁን እኛም እንወቀው፤ ሸክሙ ለምን ለናንተ ብቻ እኛም እንጋራችሁ!

ቀበና ለምን ጥሩ ወገንሽ ብቻ ይወራ? መጥፎውም ጎንሽ ይውጣ ተጋለጭ! ያኔ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት አስተዳደር ወቅት ቀበና 06 ቀበሌ ብዙ፣ ብዙ፣ በጣም ብዙ፣ አስተናግደሻል። አዎን፤ ታሪክ ሊረሣው የማይችለውን የቀይ ሽብር ዘመቻ፤ የኛው ወገን የምንላቸው ሰዎች መልሰው ለኛው ጠላት ሆነው፤ ስንቱን የቀበሌ ወጣቶች ገርፈዋል፣ አስገርፈዋል፣ ገድለዋል፣ አስገድለዋል። የስንቱን ደብዛ አጥፍተዋል፣ አስጠፍተዋል። ብዙ ለሃገርና ለወገን የሚጠቅሙ ወንድምና እህቶቻችን ረግፈው ቀርተዋል፤ ሴት ዕህቶቻችን ተደፍረዋል። በዚሁ ሣቢያ፤ ብዙ በጣም ብዙ ወገኖቻችን ይህችን አንድ መተኪያ የሌላትን ህይወታቸውን ለማዳን ሲሉ፤ በተገኘው የማምለጫ መንገድ ተጠቅመው ከሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸውና ከውድ እናት ሃገራቸው ተለይተው በዱርና ገደል ጫካና በረሃ በሰው ሃገር ለስደትና መከራ ተዳርገዋል። ስንቱም ላሰበበት ዓላማና ግብ ሳይደርስ ያውሬ ሲሳይ ሆኖ በከንቱ ቀርቷል።

ቀበና፤ ክፉ ሲሉሽ ደግ፤ ደግ ሲሉሽ ክፉ የሆንሽ፤ ቅዱስም እርኩስም መንፈስ ያለብሽ፤ ያሳደጉንን ቤተሰቦቻችንን፣ ዘመዶቻችንን፣ ጎረቤቶቻችንን፣ ጓደኞቻችንን፣ እህት ወንድሞቻችንን ለሞት አሳልፈሽ ሰጥተሽብናል። ለዚያውስ አንቺ ምን ታደርጊ የተፈጥሮ ነገር ሆኖ ነው እንጂ።

ቀበናዬ!! ህይወቴ፤ ሥምሽ ይጠራ ዛሬ! በክፉም በደጉም ታሪክሽ እንደዚህ በቀላሉ ተዘክሮ የሚያልቅ መቼ ሆነና። ልጥራሽ ጮክ ብዬ ቀበናዬ!! ቀበና 06 ቀበሌያችን ለኛ ለነዋሪዎቹዋ ልዩ! በጣም ልዩ ናት!! ለኛ ልክ እንደ እየሩሳሌም ብርቅዬ የተቀደሠች ሥፍራ ናት። ማንም ሊነካብን ከቶ አይገባም። ቀበና ከትውልድ ትውልድ ሲወራረስ የመጣ ቦታ ነው። እንደሚባለው ይህ የቀበሌ ክልል በአየር ንብረትነቱ ፍፁም ማራኪና ተወዳጅ ስለሆነ እምዬ አፄ ዳግማዊ ምኒልክ የአሁኑን የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታልን ለመገንባት እቅድ እንደነበራቸውና፤ ፍፃሜውን ሳያዩ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩም፤ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ይህንን ሆስፒታል በስማቸው ለማስታወሻ ብለው እንዳስገነቡላቸው ይነገራል። ይህም ሌላው የቀበና 06 ቀበሌ መገለጫችን ስለሆነ፤ ልክ እንደ ግብፁ ፒራሚድ በቅርስነት ሊጠበቅልንና በ06 ቀበሌ ስም ሊመዘገብልን ይገባል።

ለገሠ ዘውዴ (ከቨርጂኒያ፤ አሜሪካ)

# What is the secret behind the unity of Kebena 06's childhood friends?

Recently, my brother in law, Ato Atnafu Bekele Beyene, a strong organizer for this "Kebena 06 Kebele childhood friends' annual family reunion", called to remind me that the reunion is coming up soon. He asked me if I could make some contribution by writing a short article on any subject.

I found this request somewhat difficult due to my inexperience in writing articles. However, I accepted his request because I am a true patron of the Kebena 06 Kebele childhood friends' unity. After much thought, I decided to write this article about **The secret behind the unity of Kebena 06's childhood friends,** how they have stood resiliently and courageously together for this long.

As you might all know, I was not born in Kebena 06 but, it is where I raised three daughters and one son. I am deeply rooted to Kebena through a marriage to a well-known family, Sgt. Agonafir Demissie's family,

I lived in Kebena 06 Kebele from 1957 – 1993, Ethiopian calendar, well over 36 long years, where I should, by now, awarded a citizenship of Kebena. During all these years, I got love and respect from young or old folk, all my neighbors, Abune Gebremenfes Kidus Ider, Ye-Atebiya Kokeb Ider and generally from the community and it was really a blessing.

When one of the community or Idir members got sick or passed away, the support and visits from one another was amazing. It is hard to explain how the people of Kebena, in particular, are tied together as if we have a blood relationship to one another. Not only the people, but even Doggy Bochera has showed his loyalty. He accompanied us to the church and burial place (church), came back home to give greetings to the guests who had come to mourn, and stayed with us for three days guarding the tent during night time. This is a miracle and unique to Kebena.

What is the secret behind this myth? Who can dare to tell us this great history of our own? It's very hard to forget the Kebena 06 Kebele memories, the warm salutations that we would get as soon as we leave our house going out for picnic, family or friend's visit or simply idling around the Sholla tree, the warm handshakes, the hugging and the kissings that we exchange to one another. I remember, when we would go further up to the Entoto Woreda court house (Ded Masecha), the chat in groups, the joking, the laughter and the good smell that came to our noses through breezy winds from the surrounding Tej Bet and the delicious smell of Siga Tibis (Grill) across the street from Temesgen siga Bet. The service we get for our shoes from the young shoe shine boys (Listiro) and watching them fight (shimia) to get 0.10 or 0.20 Cents.

Then, what is the secret behind this Ye-kebena 06 childhood friends' unity? Tell us your story, don't hide from us, share your secrets today without fear, we listen to you. Tell us the secret about Kebena 06 childhood friends' in diaspora and back home leave in peace, love respect and harmony in

togetherness.

As we all know, Kebena 06 Kebele is a multi-ethnic society mix, like Amhara, Oromo, Gurage, Tigre, Somale and others inter-marrying one another, who believes in one Ethiopia and stand as a role model for others. Kebena has unknown hidden secret yet to be studied. The topography is one of the kinds, it has a lowland, a plateau and a highland. We have also the famous river "KEBENA WONZ' our Nile, and the "Dubie Bahir" as our lake Tana. One time a close friend of mine said in our Idir meeting, "even though, the people of Kebena live in a destitute level, knowledge wise, they are very talented". Yes, I share his words for my case now as a light through a tunnel for our future goals. This time, our children, grandchildren, and great grandchildren are following our footsteps. They are doctors, engineers, economists, pilots, professors, musicians and many other professionals. Who knows, one day they will show us a miracle by changing the topographical transformation of the "Dubie Bahir" to be the 2nd renaissance dam next to the Nile to generate hydro power station and sale electricity for our neighboring Kebele's, towns and cities; the topographical transformation of "Jan-hoy Meda" to a high rise building zone like Manhattan (New York), Burj Khalifa (Dubai) or like city of Singapore (Malesia). It's a matter of time, there is nothing that is impossible, this time it's all possible, we will do it YECHALAL !!.

As we know, Kebena 06 Kebele covers a small area of land with approximately 13,000 -15,000 dwellers. Historically, most of those families believed to have come here after their military services in South Korea and Congo. Any front they are mobilized, they come back to their home country after winning the war courageously. They are very good fighters and they are very well known by their bravery and heroic action they take whenever they have mission to do, and they are also award winners from the United Nations for their outstanding work on missions. They were well disciplined, well trained, and would die for their "GOAL", the motto of the lion of Juda, which symbolizes their mother land "One Ethiopia or Death". They have a lion's heart; fearless and strong, eat together and die together for one goal; victory.

Then, could this be the reason for Kebena 06 childhood friends' unity "ye-kebele yelijinet abro adeginet"? Or, this kind of atmosphere makes them always feel like togetherness as a one family wherever they go? We see them and stand as witnesses, whether it is in Australia, South Africa, European countries, America, Canada and elsewhere. We see them standing firm for their unity. Is it because, they inherited this strength from their parenthood having had a military back ground, die together for one country, one mother Ethiopia? Their high moral and power symbolizing as a role model for the new generation to come and beyond.

Kebena 06 has a rich history; both bad and good. It is remembered, during the military dictatorship era we have lost many of our iconic and brilliant children, brothers, sisters, relatives, neighbors, uncles, aunts at some point even mothers and fathers in the name of RED TERROR. Yes, they have butchered, tortured, killed and made them disappear by our own Kebele evil squads, cadres and informers. That is why most of kebena 06 kebele youths left their beloved country Ethiopia to live elsewhere all over the world.

Yet again, we have lost many of our beloved great families, neighbors, friends young and old by natural diseases that all of them now should have to be remembered this time today. Kebena 06 Kebele has a long and endless untold history yet, for us Kebena is "our Holy land" we in the diaspora will claim it one day, because for us, it is like the city of Jerusalem. It's not without reason that emperor Menilik II came to Kebena area and surveyed to build the now known hospital. As a story from the historian, this was his first plan but passed before he achieved his wishes. However, after he passed away Emperor Haile Selassie built the now famous hospital in the name of his memorial. This is our treasure and should be considered as one of the pyramid of Kebena 06 Kebele archeological museum and our ancestral burial place.

Yes, it is a natural phenomenon, who knows one day we might end up there too.

(Contributed for kebena 06 childhood friends' unity)
Legesse Zewdie (Verginia, USA)

# ስለ ቀበና የምለው አለኝ

ከዘመን ዘመን ይዘቱና ቅርጹ በትንሹ ይለያይ እንደሆን ነው እንጂ በየዘመኑ የመጡት የቀበና ልጆች አስተዳደግ፣ አዋዋል፣ ኅብረት፣ ስነምግባርና ጀግንነት ተመሳሳይ ነው። “የቀበና ልጆች አስተዳደግ” የሚባል የጽሁፍ መመርያ (ማኑዋል) ተጽፎ የታደላቸው ይመስል በየትውልዱ የመጡት የቀበና ልጆች ከህፃንነት እስከ ጎልማሳነት በየወቅቱ የሚያልፉበት የህይወት ጎዳና ተመሳሳይ ነበር። በጸደይ፣ በበጋ፣ በበልግና በክረምት ሁሉም በየጊዜያቸው ያንኑ ለወቅቱ “የተመደበውን”ወይም የሚመጥነውን ነበር የሚፈጽሙት። ለእግር ኳስ ወይም ቫሊቦል ጨዋታው፣ ለዋናው፣ ለሸርሽሩ፣ ለብይና ጠጠሩ፣ ለአክሮባትና አትሌቲክሱ፣ ለቡሄና ለእንቁጣጣሹ፣ ለጥናቱና ለተረተ ተረቱ፣ ለብሸሽቁና ለቀልዱ፣ ለድራማው፣ ለቲያትሩ፣ ለዘፈኑ፣ ለቁማሩ ለሁሉም የተመደበ ወቅት አለው\ነበረው። ዑደቱም (ሳይክሉም) አንድ አይነት ነው። በክረምት የሚደረገው በበጋ አይታሰብም። የበጋውም እንዲሁ በክረምት አይሞከርም። የአየሩ ሁኔታ፣ የትምህርት ቤት መኖር ወይም አለመኖርና እነዚህን የመሳሰሉ ሁኔታዎች ናቸው ጥንቱንም ይህን ዑደት (ሳይክል) ቦታ ቦታ ያስያዙት።

ዝንተ ዓለም በታሪክ እንደተወቀሰ የሚኖረው ወታደራዊው መንግስት መጥቶ ዑደቱን (ሳይክሉን) እስካፈራረሰው ድረስ፣ ቀበና ሠፈራችን ከተቆረቆረችበት ወቅት አንስቶ ልጆቿን ታሳድግ የነበረው (የምታሳድገው) ልክ እንደ አንድ የተደራጀ ተቋም ነበር። ልጆቿን በስነ ምግባር ማነጽ ብቻ ሳይሆን የሃገርና የወገን ፍቅር እንዲኖራቸው አድርጋ ነበር የምታሳድገው። ለዚህ ደግሞ ባለውለታዎቻችን እናት አባቶቻችን፣ ታላላቅ እህት ወንድሞቻችን ናቸው። በታሪክና በንድፈ ሐሳብ (ቲዮሪ)



ፎቶ ገዛኸኝ ታደሰ July, 2014

ሳይሆን በተግባር፣ ለሃገር፣ ለወገንና ለነፃነት መስዋዕት በመሆንና እንደነሱ ለሃገር፣ እንደነሱ ለነፃነት፣ እንደነሱ ለወገን ይቆማሉ መስዋዕትም ይሆናሉ ብለው ተስፋ በማድረግ ነበር ህይወታቸውን እየገበሩ ያስተማሩን። መቼም ውለታቢሶች፣ አደራ በሊታዎች፣ የእሳት ልጅ አመድ እንደማንሆን እርግጠኛ ነኝ። የቤትሥራውን በየልቦናችን እንጻፍና ወደ ቀበናችን እንመለስ።

የኛይቱ ቀበና፣ የኛይቱ ኮርያ ሠፈር ከላይ በክብር ዘበኛ ግንብና ከታች ደግሞ በቀበና ጅረት ታጥራ የተወሰነ መግቢያ በር የተሰራላት እስከሚመስል ድረስ ተለይታ የተቀመጠች መንደር ናት። በየአካባቢው ያሉት ሜዳዎቻችን ሐኪም ሜዳ፣ ሸክላ ሜዳ፣ ኖራ ሜዳ፣ ጃንሜዳ፣ እላይ ጫካ ሁሉም ለየእድሜ ክልሉ እንደ መዋለ ህፃናት ወይም ፓርክ ነበር የሚያገለግሉት (የዛሬውን አያድርገውንና)። ዛሬማ፣ ሐኪም ሜዳ፣ ሸክላ ሜዳ፣ ኖራ ሜዳ ወይም እላይ ጫካ ተረት ተረት ሆነዋል።

ትምህርት ቤት ከሌለ በስተቀር ጧት ቁርሱን በልቶ ከቤቱ የወጣ ልጅ ቀኑን ሙሉ ከእኩዮቹ ጋር ከነኚህ በአንዱ ቦታ ሲጫወት ውሎ ጀንበር ከጠለቀ በኋላ ጥቅጥቅ ብሎ ሲጨልም ነበር የሞት ሞቱን ወደቤቱ የሚገባው። ከእራት በኋላም ሌላ መርሃግብር አለ። ወጣ ብሎ ጥግ ይዞ ማውጋት። መተረብና መተራረብ። እድሜ ለደርግ ይህ ውብ ጊዜ፣ ይህ የማይጠገብ ወቅት ተረት ተረት ሆነ። ሞተ፤ ተቀበረ።

መንደሩ ልጆቹን የሚያሳድገው በጋራ ነበር። ወላጆች የሚቆጣጠሩትና የሚቀጡት ከአብራካቸው የወጣውን ልጅ ብቻ አልነበረም። ሁሉም የቀበና ልጅ እንደ ልጃቸው ነበር። ልጆችም እንዲሁ የሚፈሩትና የሚታዘዙት ለወላጆቻቸው ብቻ እልነበረም። ሁሉም ወላጆች እንደ ወላጆቻቸው ነበሩ። ከማለዳ ጀምሮ ሲራገጥ የዋለ ሁሉ ወደቀረበው የጓደኛ ቤት ጉራ ብሎ ምሳ ወይም እራት መቋደስ የተለመደ ነበር። ማንም የእገሌ ቤት ነው ብሎ አይሳቀቅም ነበር። አይ ጊዜ። በሮች ሁሉ ለሁሉም ክፍት ነበሩ። አሁን ሲያወሩት ተረት ተረት አይመስልም?

በነገራችን ላይ አልፎ አልፎ አንደታሪክ በነበር የማወራው ስለዛሬው መመስከር ባለመቻሌ እንጂ ቀበና ስላለፈች አይደለም።

# አብሮ አደጎች ምን ይላሉ?



ፎቶ ገዛኸኝ ታደሰ July, 2014

ቀበና አላለፈችም። ዛሬም አለች ወደፊትም ትኖራለች። ጊዜ ሲሮጥ አይታወቅምና እኔም እንግዲህ ከቀበና ከራኩኝ ከረምረም ስላለ ነው። ስለዛሬው እንመስክር ለሚሉ ታናናሾቻችን መድረኩ ክፍት ነው። የዚህ መጽሔት አዘጋጆች እጃቸውን ዘግርተው በእልልታ ይቀበላሉ። ከላይ መጀመርያ ላይ "የመጽሔቱ አዘጋጆች መልእክት" በሚለው ክፍል ላይ እኮ "ቀበናን ያላችሁ፣ እስቲ እንያችሁ" ተብሏል።

ቡሄና እንቁጣጣሽ የራሳቸው የሆነ የተለየ ታሪክና ትዝታ ነው ያላቸው። የቡሄ ዝግጅት የሚጀመረውና የሚጨፈረውም የቡሄ ዕለት አይደለም። ገና ትምህርት ቤት እንደተዘጋና ቡሄ ወር ወይም ሁለት ወር ሲቀረው ስብሰባ ማድረግ ይጀመራል። በየእድሜ ክልሉ እየተሰባሰቡ እያንዳንዳቸው በየቡድናችው እነማን በዘንድሮው የቡሄ ጭፈራ ላይ እንደሚሳተፉ ይወስናሉ። ቀኑ ሲቀርብ ደግሞ አውራጅ፣ ዳቦ ያዥ እና ገንዘብ ያዥ ይመረጣል። የቡሄ እለትም የት ቤት እንደሚታደር ይወሰናል። የቡሄ ታሪክና ትዝታ እንግዲህ የዝግጅቱን፣ የጭፈራውን፣ የአዳሩን፣ የገንዘብና ዳቦ ክፍፍሉን ገጠመኞች በሙሉ ያካትታል። በየትውልዱ የመጣው የቀበና ልጅ ሁሉ በቡሄ ዙርያ ተወርቶና ተዝቆ የማያልቅ ትዝታና ታሪክ ነው ያለው። እንቁጣጣሽም እንዲሁ። ስለእንቁጣጣሽ አፌን ሞልቼ ለመናገር ወይም ለመዘርዘር ባልችልም (ቃለ መጠይቅ ማድረግም አልሻም)። ለምን? ቢሉ የተባ ብዕር ያላቸው የቀቤ እህቶቻችንን ድርሻ ላለመሻማት ነው። ውድ እህቶቻችን፣ እስቲ ጀባ በሉን።

የገና እና የጥምቀት በዓላትም እንዲሁ የየራሳቸው የሆነ ልዩ ትዝታና ታሪክ አላቸው። አብዛኛው የጥምቀትና የገና ታሪኮች ከጃንሜዳ ጋር የተቆራኙ ናቸው። ታቦት አጅቦ ማስገባት፣ ጃንሜዳ ማደርና ታቦት መሸኘትን ጨምሮ መቼም በጥምቀት በዓልና በጃንሜዳ ዙርያ ገጠመኝ የሌለው ያለ አይመስለኝም። ግማሹ የፍቅር፣ ግማሹ የጠብ ወይም የከረሜላ ማስረገፍ፣ ሌላው ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር የቀረው ደግሞ ከፖለቲካ ተልዕኮ ጋር የተሳሰረ። ሁሉም በየፈርጁ ከጥምቀትና ከጃንሜዳ ጋር የራስ የሆነ ቁርኝት አለው።በነገራችን ላይ የቃኛው በኮርያ የስፖርት ክለብ አባላቱን በማስተባበር በጃንሜዳ የጥምቀት በዓል ላይ ትልቅ የዕድር ድንኳን በመጣል ምግብና መጠጥ በመሸጥ ለክለቡ ማሳደግያ የሚሆን ገንዘብ ያሰባስብ ነበር። ታድያ ይህ ጉዳይ በተነሳ ቁጥር በቀቤዎች አእምሮ ውስጥ የሚመላለሱት በወቅቱ ተዋንያን የነበሩት ብርቅዬዎቹ የቀቤ አብሮአደጎች፣ ገበያተኛ ለመሳብና እንደ እሳት የሚያቃጥለውን የጥቅምት ብርድ ለመቋቋምም እድንኳኑ ደጃፍ ላይ የሚቀርበው ደማቅ የዘፈን ትዕይንት እንዲሁም ድንኳንኑን ለመጠበቅ በእሳት ዙርያ ከቦ ሲያወጉ ማደር የመሳሰሉት ትዝታዎች ናቸው።

እነኚህ ሁሉ የሆኑት በግለሰብ ደረጃ አይደለም። ሁሉም በቡድን፣ ሁሉም ከባልንጀሮች ጋር እንጂ። ታሪኩ የጋራ ነው። የሚያስተሳስር፣ የሚያስታውስና የሚያነፋፍቅ። አንድም ይሁን ሁለት ትዝ የሚሉን የገና እና የጥምቀት ታሪኮቻችን በሙሉ የኛና የጓደኞቻችንም ጭምር ናቸው። ትዝታው በመጣ ቁጥር፤ ተዋንያኑም በምናባችን ብቅ ብቅ ይላሉ። ባልንጀሮቻችን።

ከላይ እንደጠቀስኩት ቀበና ልጆቿን

ታሳድግ የነበረው ልክ እንደ አንድ የተደራጀ ተቋም ነበር። እግር ኳሱ፣ አክሮባቱ፣ ቴብል ቴንሱ፣ ዋናው፣ ቫሊ ቦሉ፣ አትሌቲክሱና ሌሎችንም ውድድሮች ማድረግ በቀበና በጣም የተለመደ ነው። በተለያዩ የስፖርት ውድድሮች ቀበናን ያስጠሩም በርካታ ናቸው። ዋናው ቁም ነገር ግን እነኚህ የስፖርት ውድድሮች በቡድን መደራጀትን፣ መሠባሰብንና መተሳሰብን ግድ ይላሉ። ከሌላ ሠፈር ልጆች ጋር መወዳደር አለ። ይህ ኅብረትን፣ መተሳሰርንና መተሳሰብን ወይም አንድነትን ይፈጥራል። የወላጆች ቀንን ማዘጋጀትና ማክበርን የመሰለ እጅግ ረቀቅ ያለ ዝግጅትና ቅንብርን የሚጠይቅ ሃላፊነትን መወጣት የቀበና ልጆች የተካኑበት ነበር። የቀበና ልጆች በቡድን በቡድን ተከፋፍለው፣ የተለያየ ስም ይዘውና መለያ ለብሰው ነበር የዋንጫ ውድድሮችን የሚያካሂዱት። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ማለፍ ደግሞ ምን ያህል ፍቅር፣ ትስስርንና ኅብረትን እንደሚፈጥር መገመት እያቅትም።

ከዚህ አልፎ ተርፎ፣ እንደ ቃኛው በኮርያ ዓይነት ሁለገብ ማኅበር\ክለብ ማቋቋምና በሥሩም ስፖርት፣ ስነጽሁፍ፣ ዘፈን፣ ውዝዋዜና ድራማን የመሳሰሉ የተለያዩ የቀበና ልጆች እንደ ፍላጎታቸው የሚሳተፉባቸው ክለቦችን መመሥረት አንድ በውል የተቋቋመ ወይም የተደራጀ አካል ካልሆነ ማንም ይሞክረዋል ተብሎ አይታሰብም። ነገር ግን ይህ ሁሉ በኛይቷ ቀበና ተፈጽሟል። በርካታ የስፖርት ውድድሮች ተደርገዋል፤ ምርጥ ምርጥ ድራማዎችም ለቀቤና ለአካባቢው ኅብረተሰብ ቀርበዋል። ጉድም አሰኝተዋል።

በራስ አነሳሽነት እነኚህን የመሳሰሉ ትላልቅ ተግባራትን መፈጸም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ራሳቸው "በዲሞክራሲና" በስምምነት የመረጧቸውን የማህበሩና የክለቦች መሪዎችን ትእዛዝ እያከበሩ ኮሽ ሳይልባቸው ለውጤት ለመብቃት ታላላቆችን ማክበርንና መታዘዝን፣ ትልቅ ዲሲፕሊንና በደንብ ታርቆ\ተቀጥቶ ማደግን ይጠይቃል። ላወቀበትማ እንዲህ አይነቱ ፍቅርና መከባበር ነበር እኮ ሁሉን የሚገዛ። ይህ አይነቱ ሰነምግባርና ውጤታማነት ደግሞ አርአያነቱ ፈጽሞ በገንዘብ የሚተመን አይደለም።

የቃኛው በኮርያ የስፖርት ክበብ ከቀበና ርቆ ያደርግ የነበረው የስፖርት ውድድሮችን ብቻ አልነበረም። የድራማ፣ ዘፈንና ውዝዋዜ ዝግጅቱን ይዞ ራቅ ያሉ ቦታዎች ድረስ በመሄድ ለተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ያቀርብ ነበር። ለዚህ አንዱ ምስክር በሆለታ ገነት የጦር አካዳሚ ያቀረበው ታላቅ ዝግጅት ነበር። አይገርምም? እንዴት ያሉ አርቲስቶችን አፍርቶ ነበር? ያ ከላይ ያነሳሁት የታሪክ ተወቃሽና ዝቃጭ መንግስት መጥቶ ባይበታትነው ኖሮ፤ ይህ ክለብ የት ይደርስ እንደነበር መገመት አያዳግትም። እነኚህን የመሳሰሉ ዝግጅቶችን ለማቅረብ የሚደረግ ልምምድ፣ ጉዞውና አፈጻጸሙ ሁሉም ታሪክ፣ ሁሉም ትዝታ አላቸው። ይህ ደግሞ የሚፈጥረው ትስስር፣ ፍቅርና መተሳሰብ ዘመን የማይሽረውና በጊዜ ርዝመት የማይደበዝዝ ትዝታና ውህደት ፈጥሯል ። የነበሩ ይናገሩ።

ሌላው የሚገርመውና ከመተሳሰሪያችን ሚስጥሮች አንዱ የሆነው ደግሞ የቀበና ታላላቆቻችን የክረምት ትምህርት ቤት እየከፈቱ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግና ደከመን ሰለቸኝ ሳይሉ የራሳቸውን ወንድም እህቶች በማስተማርና በማስጠናት አሁን ትላልቅ ቦታ ለደረሱት የቀበና ልጆች የማይናቅ አስተዋጽዖ ማድረጋቸው ነው። በህይወት ያሉትም ሆነ ወደ እውነተኛው ቦታ የሄዱት ሁሉም ምስጋና ይግባቸው። በዚህም ዙርያ ዝንተ ዓለም የማይረሱ ትዝታዎች አሉን።

እንግዲህ ሁሉም እንደሚገነዘበው፤ ያ ሳይታሰብና ሳይገመት እንደተቋረጠ ሲኒማ ቁምጥ ብሎ የቀረውን ዑደት ማጠናቀቅ ትዕይንቱንም ማየት እንፈልጋለን። የጎደለ አለና ልንሞላው እንሻለን። ከአጠገባችን የተነጠቁ አሉና እንናፍቃለን። ውድ ውዶቹ አጠገባችን የሉም። በሕይወት ያሉትም እርቀዋል። እናም ዛሬም፣ ነገም፣ አምናም፣ ዘንድሮም፣ ለከርሞም፣ ቀንም፣ ማታም ሁሌም በጆሮአችን፣ በአዕምሮአችን ያቃጭልብናል። ይጮህብናል። ሐኪም ሜዳ ወይም ኖራ ሜዳ የተቋረጠውን ያንን የመጨረሻውን ጨዋታ ተመልሳችሁ ጨርሱ፣ አጠናቁ ይሉናል። የመጨረሻውን ውጥን አከናውኑ ይሉናል። በጅምር የቀረ ጉዳይ ስላለ ሁሌም ጎዶሎነታችን ይሰማናል። ይህን ጉድለት የሚሞላ መድሃኒት ደግሞ አልተፈበረከም። መፍትሄው አንድ ብቻ ነው። እርስ በርስ መተካከም። እናም በሽታችንን እርስ በርስ ለመተካከም እንፈላልጋለን። በሄድንበት፣ በደረስንበት ሁሉ ቀበና፣ ቀበና የምንልበት ምክንያትም እንግዲህ ይሄው ነው። ይህ መፈላለግ የወለደው ነው እንግዲህ የቀበና አብሮ አደጎች ስብስብ።

እንደው ጠቅለል ባለ መልኩ ማቅረብ ካስፈለገ የቀበና\ኮርያሰፈር ህዝብ አኗኗር ለአስተዳደርና ለቁጥጥር እንዲመች ተብሎ በንዑሳን ቤተሰቦች ተከፋፍሎ፣ ነገር ግን በአንድ ትልቅ ጣራ ስር የሚተዳደር ነበር የሚመስለው። ወላጆች ሁሉንም ልጆች እንደራሳቸው ያያሉ፣ ይንከባከባሉ፣ ይቆጣሉ፣ ይቀጣሉ። ልጆችም እንዲሁ፤ ሁሉንም ወላጆች ያከብራሉ፣ ይወዳሉ፣ ይታዘዛሉ። በሮች ሁሉ ለሁሉም ክፍት ነበሩ። ሁሉም ተከባብሮ፣ ሁሉም ተዛዝኖ፣ ሁሉም ተካፍሎ ነበር የሚያድረው። ዓመትባል መጣ ከተባለ፤ አንዱ ጋ ምሳ፣ ሌላው ጋ ደግሞ እራት ሲባል ቀናት ይቆጠሩ ነበር። ያንዱ ሃዘን የሁሉም ነው። ያንዱ ደስታም እንዲሁ። ሰርጉንም ሆነ ለቅሶውን ሁሉንም በጋራ ነው የሚወጡት። ታድያ ከዚህ በላይ ቤተሰብነት፣ ከዚህ በላይ አንድነት ከወዴት ይመጣል? ግልጽ ነው? ተሳስቼ ይሆን እንዴ? መቼም ያቅሜን መሰንዘሬ፣ የማውቃትን መሞነጫጨሬ ክፋት ያለው አይመስለኝም። እርማትም ካለ፤ ተጨማሬም ካል፤ ማብራርያም ካለ፤ እሰየው ነው። "ቀበናን ያላችሁ፣ እስቲ እንያችሁ" ተብሏልና። እጃችሁ ከምን?

እንደ ቸርነቱ ብዛት፣ የከርሞ ሰው ይበለን።

ቆለኛው

# የልጆች ዓምድ





ይህ አምድ የሠፈራችን የልጅነት ትዝታ የሚወሳበትና ልጆቻችን ስለኛ ምን ይላሉ ምንስ ከእኛ ተማሩ በሚሉት ጥያቄዎች ዙርያ የሚሰማቸውን ስሜት እንዲገልጹ የተዘጋጀ አምድ ነው። ባለፈው ዕትም ላይም በዚህ አምድ ስር ሁለት ወጣት ልጆች የሚሰማቸውን ገልጸውልናል። ዘንድሮ ደግሞ ሌሎች ሁለት ወጣቶች ፣ ሁለት ተረኞች፣ ሁለት ባለሳምንቶች ጽሁፋቸውን ይዘው ቀርበዋል። ጽሁፋቸውን ከማቅረቤ በፊት እኔም በመንደርደርያነት ስለ ቀበናዬ ትንሽ ለመጫር ተነሳሳሁ።

ቀበና (ኮሪያ ሠፈር) ከተቆረቆረች ከ1950 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ ብዙ ወጣቶችን አፍርታለች። አብዛኛዎቻችንም ለአባወራነትና እማወራነትም ደርሰናል። አልፈናልም። ወላጅ ቤተሰቦቻችን ከተለያየ ቦታ መተው ኮሪያ ሠፈርን መስርተው አሻራውን ሲያኖሩ፣ ቁጥቋጦውን እየመነጠሩ ገደሉን እየሞሉ ሠፈሩን ቆረቆሩት። ለሚወለደውም ትውልድ ምን እንደሚያስፈልገው የተረዱት ወላጆቻችን ከህሁ መቁጠሪያ እስከ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ድረስ ገነቡ (መሠረቱ)። ለዚህ ሁሉ ዋና መሠረት የሆነው ፍቅር፣ ሰላምና መተሳሰብ ስለሆነ ለኛም ለልጆቻቸው ይህንን ችሎታቸውን አስተማሩን።

ሠፈራችን ቀበና\ኮሪያ ሠፈር ባንዳንድ ማስታወሻዎች (Land Mark) ምክንያት በተለምዶ በሚጠሩ አምስት ትናንሽ መንደሮች የተከፋፈለች ነች። እነርሱም ሸክላ ሜዳ፣ ሾላ ሠፈር፤ ቦኖ ውሃ፣ ካምፕ ግቢ፣ ሃኪም ሜዳ (ጐጃም ሠፈር) እና ሚሽን ሠፈር ናቸው። ከትዝታዎቻችንም በጥቂቱ መግለጽ ካስፈለገ፣ ከላይ በተጠቀሱት መንደሮች ተከፋፍሎና በአንድነት የሚደረጉት የስፖርት፣ የቲያትር፣ የዘፈንና ሌሎችም ውድድርና ፉክክሮች፣ አብረን ሀሁ የቆጠርንባቸው የየኔታ ት/ቤትና የአንደኛ ደረጃ ትምህርታችንን የተከታተልንበት የእድር ት/ቤት ናቸው። እነዚህ አብረን የዋልንባቸው ጉዳዮች ሁሉ እንድንዋደድ፣ እንድንፋቀርና እንድንፈላለግ አድርገውናል።

ዛሬ ደግሞ ያ ትዝታ እንቅልፍ ነስቶን በሃገር ውስጥ፣ በአሜሪካና በተለያየ ዓለም ያለነው ተሰባስበን ለአራተኛ ጊዜ በተከታታይ በሚያሳዝነው እያዘንን፣ በሚያስደስተው ደግሞ እየተደሰትን፣ ወደፊትስ ምን እናድርግ እያልን እንገኛለን። ታዲያ ይህን ሁሉ ትዝታ፣ ፍቅርና መተሳሰብ እኛ ከቤተሰቦቻችን ወረስን፣ የኛ ልጆች ደግሞ ከኛ ምን ይማራሉ? ስለ እኛስ ምን ይላሉ? ወደፊትስ የኛን አርአያ ይከተሉ ይሆን? በማለት ይህ አምድ ተከፍቶ ከዚህ በፊት ሁለት ወጣቶች ልምድና አስተያየት አካፍለውናል።

ዛሬ ደግሞ ሁለት (የ11 ዓመትና የ16 ዓመት) ልጆች እንደዚሁ የራሳቸውን አስተያየት ለመስጠት ፈቃደኞች ስለሆኑ እነሱን እያመሰገንኩ ከነሱ የተዘጋጀውን ፅሁፍ እንድታነቡ እየጋበዝኩ፤ ቸር ይግጠመን እያልኩ፣ ወደፊት በሰፊው ስለ ሰፈራችን የልጅነት ትዝታ ለማቅረብ ቃል እየገባሁ፣ ከዚህ በታች የተቋጠረችውን ስንኝ ጀባ ብዬ እሰናበታለሁ።

ከቀበና በላይ
ከጃንሜዳ በታች
　　በኮርያ ሰፈር
　　ትዝታው ብዙ ነው ለሚያንጐራጉር
ኖራ ሜዳ ሄደን
ሃኪም ሜዳ ሄደን
　　ቀበናም ወርደን ኳስ ልንጋጠም
　　ዛፍ ላይ ተንጠልጥለን
　　ከገደል ላይ ወተን
ስፖርትን ስንሰራ
ጡንቻን ለማጠንከር ለማስከበር ጐራ
　　ያ ትልቁ ዋርካ ሾላዬ ሾላዬ
　　ያ መጠለያዬ
ያ መደበቂያዬ
ፍሬውን በልቼ ዛፉ ማረፊያዬ።

አጥናፉ በቀለ

# Reunion

We would like to say thank you to Yekebena group for giving us this opportunity to write about what we are feeling about the reunion. We really loved these past reunions! We've enjoyed them so much! My dad told me that some of you haven't seen each other for a long time. We met so many people we never even knew that they were in our family. We made so many friends; and it's amazing how our parents stuck together after having not seen each other in such a long time. It's a beautiful thing when your whole family is together and they're happy and having so much fun. My favorite part was when we met up at the park and it was really fun playing on the playground with my friends and family.

We never expected that many people from different states and countries like Canada, Chicago, Virginia, London, and even Ethiopia to come all the way here for the family reunion. I also enjoyed looking back at the pictures because I know that those pictures will show our family's history to our future kids, so they will know it too. I once visited Kebena too when I was younger, but I have no memory of it because I was less than a year old. But my older brother was old enough to remember it and how it was. He told me all about it. He told me about all the fun he had with our family and friends while we were there. After he told me about his time there, it made me really want to visit again and hope to be able to continue stay close to all of my family and friends from Kebena as we all grow older too. I'm happy and proud that I'm Ethiopian; I would like to invite my brother Yeneneh to share his memory about Kebena.

*Matthewos Atnafu Bekele Beyene Habtewold*

My Name is Yeneneh. As my brother Matthewos mentioned above, I got a chance to visit Kebena for two short and sweet months, walk around Korea Sefer neighborhood where you guys were born, and grew up. I saw your elementary school, the river where you guys practiced swimming, where you relaxed, and the place you played soccer. It was a good time and I met a lot of kids and I had a lot of fun



*Matthewos*


*Yeneneh*

with them. Also I tried to learn the Amharic song "Lambadina" with a lot of kids in my grandma's house. For the first time in my life, it was little bit difficult to understand others, but those kids were trying to communicate with me in English and I wanted to learn Amharic too. Some of them spoke good English and I was surprised. The kids were very friendly and the people were very kind. Now I truly understand and appreciate Ethiopia's great culture and know more about Kebena, the first and second generation. You, our parents, gave the kids, a chance to meet and get to know the rest of the future generation of Kebena. I met a lot of people from different states and we had a great time every year for the last three years, also we started playing games online with each other and got the chance to exchange some information. Another thing I noticed is that the culture of support and getting together when both happy and sad times or moments. Recently one of your brothers passed away, you all from Kebena came together and shared the sorrow with the family.I was also able to attend the church and funeral ceremony. To finalize my writing, I would like to ask the new generation (my age group) to meet each other, share our experiences, and eventually take over and continue this beautiful culture of love and support that our parents already have for one another. It is time and what do you think?

*Yeneneh Atnafu Bekele Beyene Habtewold*

# እስቲ እናስታውሳቸው



## የሰለሞን ሐድጉ ንጉሴ (ጋንፋር) አጭር የህይወት ታሪክ

### ከ1948 ዓ.ም - 2008 ዓ.ም

ሰለሞን ሐድጉ ንጉሴ (ጋንፋር) ከአባቱ ከባላምባራስ ሐድጉ ንጉሴና ከእናቱ ከወ/ሮ ብዙነሽ አምዴ እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ግንቦት 16 ቀን 1948 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ስድስት ኪሎ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ተወልዶ ቀበና ወይም ኮርያ ሰፈር ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ አደገ። ሰለሞን ከልጅነቱ ጀምሮ እጅግ ይወዱትና ይሳሱለት በነበሩት አያቱ እማሆይ ተዋበዛሽ በማቆላመጥ ባወጡለት ስሙ “ጋንፋር” በመባል ይጠራ ነበር። አያቱ ይህን ስያሜ የሰጡት መልከ መልካምነቱንና ድንቡሼነቱን በማየት ነበር። ለቤተሰቦቹ 5ኛ ልጅ የሆነው ጋንፋር ዕድሜው ለትምህርት እንደደረሰ በቀድሞው ደጃዝማች ወንድይራድ ትምህርት ቤት በመግባት የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሏል። በመቀጠልም ወደ ኮከበ ጽባሕ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (ቀ/ኃ/ሥ) ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርቱን የተከታተለ ሲሆን በትምህርት ቤት ቆይታውም በስካውት ክበብ ውስጥ በመሳተፍ የተለያዩ ክህሎቶችን ቀስሟል። በስካውትነት እስከ ፓትሮል ሊደር (ኃላፊ) ሆኖ አገልግሏል። ይህንንም ዕውቀት በማዳበር ለት/ቤቱም ሆነ ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል በጥሩ አርአያነቱ ሊያሳውቀው በሚችል መልኩ አስፈላጊውን አስተዋፅኦ ያደረገ ታላቅ ሰው ነበር።

ጋንፋር ባደገበት ቀበና ኮርያ ሰፈር “የሕዝብ ልጅ” በመባል ነበር የሚታወቀው። በአዛውንቱ፣ በወጣቱም ሆነ በሕጻናቱ ሕይወትና ልብ ውስጥ ጋንፋር ማለት ደስታ ማለት ነበር። እርሱ ያለበት፣ እርሱ የገባበት ማንኛውም ማህበራዊ ዝግጅትና ስብስብ ሁሉ ይሞቃል፤ ይደምቃል። መቸም ጋንፋርን ሳይስምና ሳይመርቅ የሚያልፍ እናት በሰፈራችን አልነበረም። እናቶቻችንም ከገበያ ሲመለሱ እቃቸውን ተሸክሞ ከቤታቸው ድረስ በማድረስ ጋንፋር የታወቀ ወጣት ነበር፡፡ የጋንፋር ሌላው አስደናቂ ችሎታው ደግሞ ደስታንና መዝናናትን በሰዎች አእምሮ ውስጥ የመናኘት ልዩ ተሰጥዖው ነበረ። በልጅነታችን የአካባቢው ወጣቶች “ቃኘው በኮሪያ” በሚል ስያሜ አቋቁመውት በነበረው ማህበር ውስጥ የጋንፋሬ አስተዋጽዖ ጉልህ ነበር። በማህበሩ የመዝናኛ ዝግጅቶች ላይ ጋንፋሬ ያላጀበው ዘፈንም ሆነ ድራማ ድምቀት አይኖረውም ነበር።

ዕድሜው ገና ለጋ በነበረበትና የወሎ ክ/ሀገር በድርቅ በተመታበት ወቅት፤ እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በ1965 ዓ.ም ክረምት ወራት ውስጥ ከስካውት ክበብ ባልደረቦቹ ጋራ በመሆን በበጎ ፈቃደኝነት ቦታው ድረስ በመሄድ ለተቸገሩ ወገኖቻችን ምግብ በማከፋፈልና በህመም የተጎዱትን እርዳታ እንዲያገኙ በማድረግ ለወገን ደራሽነቱን አስመስክሯል። ለዚህ መልካም ስነምግባሩም የምስጋና የምስክር ወረቀትና የመጽሀፍ ሽልማት ተበርክቶለታል።

በጊዜው በነበረው አስተዳደር በታወጀው የዕድገት በኅብረት ዘመቻም እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ጥር 10 ቀን 1967 ዓ.ም ወደ ነገሌ ቦረና ዘምቶ ነበር። በዘመቻውም ቦታ ገበሬውንና የአካባቢውን ሕብረተሰብ በማስተማርና የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ከማበርከቱም በላይ፣ በጊዜው በነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ጀምሮ መሬት ላራሹ የሚለውን የወቅቱን መፈክር ይዞ ተነሳ። በዓይን ምስክር የሆነለትን የደሀውን አርሶ አደር ኑሮ ለመቀየር በሚደረገው ትግል ውስጥ እራሱን እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ አሳልፎ ለመስጠት ቃል ገባ።

ሰለሞን ጋንፋር ወታደራዊው አምባገነን መንግስት (ደርግ) በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደርስ የነበረውን ጭካኔ የተሞላ ኢሰብዓዊ ጭፍጨፋና ግፍ፣ የአስተዳደር ብልሹነትና ሙስናን በመቃወም ወደ ትግል የወጡትን ምሁራንና ወጣቶችን በመቀላቀል በአዲስ አበባና አካባቢዋ ይደረግ በነበረው ሰላማዊው ትግል፤ በጎንደርና በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ በተደረጉት የትጥቅ ተጋድሎዎች ላይ በልበሙሉነት በመሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህ የሞት የሽረት ትግል ጉዞውም በአዲስ አበባ ከተማ በደርግ ታጣቂዎች በተለያዩ ጊዜያት እስርና እንግልት እንዲሁም ጉዳት ደርሶበት የነበረ ቢሆንም ይህ ከትግሉ ሳያግደው በቆራጥነት ትግሉን የበለጠ ለመቀጠል ወደ ጎንደር በመሄድ የትጥቅ ትግሉን ተቀላቅሏል።

በከተማ የሚደረገው ሰላማዊው ትግል ከፍተኛ አደጋ ላይ በወደቀበት ጊዜና አምባገነኑ መንግስት በሕዝቡና በተቃዋሚ ሀይሎች ላይ የሚያደርሰውን ግፍና በደል በማጠናከር ወጣቱን በማሳደድ እስራት ግርፋትና ግድያውን ተያያዘው። ጋንፋርም በከተማ መቆየቱ ለከፍተኛ አደጋ ስላጋለጠውና ክትትሉም እየጨመረ በመምጣቱ በወቅቱ በሰሜናዊው የሀገራችን ክፍል የትጥቅ ትግል ያካሂድ የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊትን (ኢሕአሠ) ጠለምት ላይ እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በ1969 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ተቀላቅሏል። በተለያዩ ጦርነቶችም ላይ ተካፍሏል። ወደ ጎንደር በሚጓዝበት ወቅትም ደጀን ከተማ ሲደርስ ከፍተኛ ችግር ቢያጋጥመውም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ከታጣቂዎች በማምለጥ ጎንደር ከተማ ገብቷል። ሠራዊቱ በጋይንት አውራጃ ሰፍሮ በነበረው የደርግ ሠራዊት ላይ በአደረገው የማጥቃት

ዘመቻ ብዛት ያላቸውን የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን የማረከ ሲሆን ፥ ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነትም የተከፈለበት ጦርነት ነበር። ብዛት ያላቸው የሠራዊቱ አባሎችም ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ሲሆን ጋንፋርም ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶበት ለረጅም ጊዜ በህክምና ሲረዳ ቢቆይም ቁስሉ በቀላሉ ሊድን አልቻለም። በመጨረሻም ከረጅምና አድካሚ ጉዞ በኋላ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1980 ዓ.ም ወደ ሱዳን ተሰደደ። ታላቅ ወንድሙ (አዝመራ ሐድጉ) በአሜሪካ ይኖር ስለነበር እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1981 ዓ.ም ወደ አሜሪካ መጥቶ አዲሱን ኑሮውን ተያያዘው።

ጋንፋር የአሜሪካ ህይወቱን የጀመረው ከታላቅ ወንድሙ ጋራ አብሮ በመኖር ሲሆን በወቅቱም በአንድ ክለብ ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ ነበር። ቀጥሎም እዛው በሚኖርበት ቦታ ከተዋወቀው ጓደኛው ጋራ በደባልነት (ሩም ሜት) ሆኖ ኖሯል። ስራውንም ቀይሮ ሆሊዴይ ኢን በሚባል ሆቴል ተቀጥሮ ሰርቷል።

የጋንፋር የምንጊዜም ታላቅ ሕልም ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ ተመልሶ ሕዝቡን ለማገልገል ስለነበረ ለዚያም የበለጠ ይረዳው ዘንድ ወደ ት/ቤት ተመልሶ ትምህርቱን በመቀጠል የምህንድስና ሙያ ለማጥናት ስለነበር፤ ስራውንም እየሰራ ትምሕርቱን በዩዲሲ (UDC) ሲከታተል ቆይቷል።

እንደምናውቀው ጋንፋር በሄደበት ቦታ የሁሉም ወዳጅና ጓደኛ እንደነበረ ሁሉ፤ በአሜሪካም ከተዋወቃቸው ጓደኞቹ ጋር በመሆን ከ30 ዓመታት በፊት የመረዳጃ ማሕበር አቋቁመዋል። የመረዳጃ ማሕበሩ እስካሁን ለአባላቶቹ ከፍተኛ አገልግሎቶችን እያበረከተ ሲሆን፤ የመስራቹንም የጋንፋርን የቀብር ስነስርዓት በሚያኮራ ሁኔታ አስተናብረዋል።

ጋንፋር የልጆቹን እናትና ውድ ባለቤቱን ኤልሳቤጥን ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀው በዋሽንግቶን ዲሲ 18ኛው መንገድ ላይ ይገኝ በነበረው የፋሲካ ሬስቶራንት ውስጥ ነበር። ከተዋወቁም ከአንድ ዓመት በኃላ ትዳር መስርተው እየሩሳሌምን፣ ቤተልሔምንና ነብዩን አፍርተዋል። ጋንፋር ትዳሩንና ልጆቹን በጣም ከመውደዱ የተነሳ፤ ይጓጓለት የነበረውን የምሕንድስና ትምሕርቱንና ስራውን አቋርጦ ትኩረቱን ለልጆቹ ለመስጠት እንዲያስችለው የታክሲ ስራ ጀምረ። ልጆቹንም በጥሩ እንክብካቤና ስነምግባር አሳድጎ ለቁም ነገር በማብቃቱ ምክንያት 1ኛ እየሩሳሌም ሰለሞን እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በሜይ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ከሉዚያና ስቴት ዩንቨርሲቲ በማስተርስ ዲግሪ፣ 2ኛ ቤተልሔም ሰለሞን በሜይ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ከቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ ዩኒቨርሲቲ በቢኤ ዲግሪ፣ 3ኛ ነብዩ ሰለሞን በጁን 20 ቀን 2016 ዓ.ም ከአናንዴል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመርቀዋል።

ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ሀገሩን የማየት ሕልሙ ምንጊዜም በልቡ ተቀብሮ ያስጨንቀው የነበረው ጋንፋር፤ ሀሳቡ ተሳክቶለት በአሜሪካ ከተዋወቀው የመጀመሪያ ጓደኛው ጋር በመሆን እአዘአ በ2004 ዓ.ም የሚወዳትን የእምዬ ኢትዮጵያን መሬት እንደገና ረገጠ። እንደ ልጅነቱ ሁሉ፣ በቀበና ኮሪያ ሰፈር በየመንደሩ በመዞር እያንዳንዱን ቤት እያንኳኳ ሰላምታ አቀረበ። በትግል ያጣቸው የጓዶቹን ቤተሰቦችም አፅናንቶና የሚችለውን ደጓጉሞ ተመለሰ።

በ 2013 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ከቀበና አብሮ አደጎቹ የቀረበውን የመሰባሰብ ሀሳብ “የተቀደሰ ሀሳብ ነው” በሚል ተቀብሎና የመጀመሪያው የዝግጅት መሪ በመሆን ለረጅም አመታት ተለይቷቸው ከነበሩት ብዙ የቀበና/ኮርያ ሰፈር አብሮ አደጎቹ ጋራ ሰኔ 1 ቀን 2006 (ጁላይ 6 ቀን 2013) በ ሲልቨር ስፕሪንግ ሜሪላድ ተገናኝቶ ናፍቆቱን ተወጥቷል።

ለዚሁ የመጀመሪያው የአብሮ አደጎች የመሰባሰቢያ ቀን ዝግጅት ጋንፋር በዋናነት መላውን የቤተሰብ አባላቱን አሰማርቶ፤ ገንዘብ ንብረቱን ሁሉ አፍስሶ የደመቀ ዕለት እንዲሆን አድርጓል። ዝግጅቱን በዋና አዘጋጅነት መራ፤ አስተባበረ። ራቅ ካሉ ሥፍራዎች ለዝግጅቱ የመጡትን በቤቱ ተቀብሎ አስተናገደ። ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ዝግጅቶችንም እንዲሁ የሞቁ፤ የደመቁና የተሳኩ እንዲሆኑ አደረገ። ጋንፋር፤ የቀበና አብሮ አደጎች የመሰባሰብ ሂደት ማዕከል ነበር፤ ድንኳናችን ነበር። በእያንዳንዳችን የግልም ሆነ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ልዩ ስፍራ ነው ያለው። ጥሎ ያለፈው የበጎ ሥራ አሻራም የዋዛ አይደለም። ሰለሞን (ጋንፋር) ከቤተሰብ፣ ከወዳጅ ዘመድ፣ ከጓደኞቹ እና ከትግል አጋሮቹ ጋር በመከባበር፣ በመቻቻልና በመግባባት መኖርን ያሳየ፣ ሰው አክባሪ፣ ለችግር ደራሽ፣ በማህበራዊ ህይወቱ ጠንካራ፣ ጨዋታ ወዳድና አስተዋይ ሰው ነበረ።

ጋንፋሬን እንግዲህ ተሰናብተነዋል። እሱ ወደ እውነተኛው ቦታ ሄዷል። በሃዘንና በለቅሶ ብዛት ቢሆን ኖሮ ዛሬ ጋንፋሬ ተመልሶ በመሃላችን በሆነ፣ የልጆቹን ምርቃት በተካፈለ፣ ኤልሲን ምን ልታዘዝ ባለ ነበር። ይሄ የኛ የሰው ልጆች ምኞት ነው። እውነታው ግን ለየቅል ነው። ቀይ የትራፊክ መብራት ያቆማቸው በአራት መንታ መንገድ ላይ በየወገኑ በየአቅጣጫው የሚጠባበቁ መኪኖች ደቂቃውንና ተራቸውን እየጠበቁ አረንጓዴው ሲበራ እንደሚሄዱት፣ እንደሚሮጡት አይነት ነው የኛ ነገር። አረንጉዴው ሲበራ። ሰንጠራ፤ መሄድ ብቻ ነው። ቁም ነገሩ ግን፣ ከዚያ በፊት ምን አድርገናል ነው። እንደ ጋንፋሬ ሰው መውደድና ለሰው መሞትን ባህላችን አድርገናል ለወገን እንድረስ ብለናል እህት ወንድሞቻችንን ፈልገናል ላሳደገን ለባለውለታችን ደርሰናል ልጆቻችንን ለወግ ለማዕረግ አብቅተናል ቤተሰባችንን ትዳራችንን ተንከባክበናል ወላጆቻችንን አክብረናል ይህ ነው እንግዲህ ጥያቄው። ይህ ነው የጋንፋሬም አደራ። ይህ ነው እሱንና መሰል አጠገባችን የሌሉ እህት ወንድሞቻችንን፣ እናት አባቶቻችንን የሚያስደስተው። የጋንፋሬን ሃዘን በልባችን እንደያዝን ሁሉ የሱንም በጎነት፣ ለሃገር ለወገን ሟችነት መውረስ ይጠበቅብናል።

እግዚአብሔር ነፍሱን በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ አጠገብ ያሳርፍልን፤ ገነት መንግስተ ሰማያትን ያውርስልን፤ አሜን።

ለዚህ አጭር የሕይወት ታሪክ አስተዋጽዖ ያደረጉት
ከተማሽ ንጉሴ፣ ደመቀ ጀምበሬ፣ ግርማ ታደሰ፣ ሰለሞን አስፋው፣
ወርቁ ዳመና፣ ዲናው መንግስቱ እና ገዛኸኝ ታደሰ ናቸው።



# የሃዘን መግለጫዎች

## የኮርያ ሠፈር አብሮ አደጎችን በመወከል የወጣ የሐዘን መግለጫ

የባላምባራስ ጎድን ደግሞም የብዙነሽ
የአዝመራና የአበራ አስታዋሽ
የከቴና የአልማዝ ታናሽ
ሰለሞን ጋንፋሬ የቀበና አስታዋሽ
በዛ በሰቆቃ በዛ ውጅንብር በድንገት የወጣው
ከወጡት ስደተኞች አንዱ ጋንፋሬ ነው።
የቃኘው በኮርያን መድረክ የሚያሞቀው
ኮከበ ፅባህ ሲማር የልጅ እስካውት ነው።
ትንሹም ትልቁም ሁሉም የሚወደው
ሁለገብ ጋንፋሬ የቀበና ልጅ ነው።
ውብ ዓለም ታምሩ፣ ብርቱካን መኮንን
ገነት ተረፈና እቴነሽ ሰይፋ ሆነን
ጨኑና ቡጡቃ ቀበናን አንስተን
የጠፋና የሞተ የተሰደደውን
የስማቸውን ተራ ስንኝ አስገብተን
የቀበና ምንጩ ወንዙ እንዳይደፈርስ
የተሰደደና የወጣው ይመለስ
እያልን እንዘፍን ነበረ እንባችን እስኪፈስ።
የቀበና ውሃ አረንጓዴ አትልበስ
ምን ይጠጣል ጋንፋሬ በድንገት ቢመለስ።
ተብሎ ቀበና የተዘፈነለት
ሽማግሌ አሮጊት ወጣት ያዘነለት።
ቀበና ሚኒሊክ ሸክላ ሜዳ ሁሉ
ከሐኪም ሜዳ ተነስቶ ጀርመን ድልድይ ያሉ
ከሾላው ጥላ ስር እስከ ወንዝ አካሉ
በድፍን ቀበና ኮርያ ሠፈር ሁሉ
ከተወዳጆቹ በተለይ ነባሩ
ሲያዝኑ ከረሙ ጋንፋር ሞተ እያሉ።
የጋንፋር መዋኛ የዱቤ ባህር
ሚስጥርህን አውጣ፣ እስቲ ተናገር
ከጃንሜዳ አንስቶ በሚሽን ሠፈር
በቃዲደጅ አልፎ በአባ አብደላ በር
ጋንፋሬን ለማሰር ይታሰስ ነበር።
በስደት በበረሃ በችግር ያልሞተው
አብሮ አደጉ ጓዴን ዛሬ ምን አገኘው።
በልጅነታችን በቀበና ውሃ የተረጫጨነው
ሜዳ ላይ ጢ.ብ ጢ.ብ ቆርኪ የተጫወትነው
ገመድና አባሮሽ ጠጠር የመታነው
ምኒሊክ ሆስፒታል ዘለን የምንገባው
ሠርግና ጭፈራ ገብተን ምንዘፍነው
ቡሄና እንቁጣጣሽ አብረን የጨፈርነው
የጊዮርጊስን ፅዋ አብረን የጠጣነው
ሊረሳኝ አልቻለም ዛሬም ፊቴ ላይ ነው።
ከሁሉም ከሁሉም ከፊቴ የማይጠፋው
ጋንፋሬ ለእንቁጣጣሽ አብሮን ጨፋሪ ነው።
ሁለገብ ጋንፋር ለሁሉ እሚደርሰው
ሰው ተራብ ብሎ አደባባይ ቆሞ እንባውን የሚያፈሰው
ከራስ ምቾት ይልቅ ለሕዝብ አብልጦ ነበር የሚቆመው፣
የሚቆረቆረው።
የእናት የአባቱን ቤት ጥሎ የኮበለለው
ወንዱ ጀግናው ጓዴ ሲፈለግ የጠፋው
በመላው ኢትዮጵያ ስሙ የተናኘው
በዛ ክፉ ጊዜ ሮጦ ያመለጠው
በሰላሙ ጊዜ ሞት እንዴት አገኘው?
አብሮ አደጉ ሁሉ ከቴን አላቀሳት
እንደው በሰው ሀገር አልማዝን ምን ዋጣት?
ይብላኝ ለእታብዬ ለምትሳሳው
ይብላኝ ለከተማሽ ለናፈቀችው
ይመጣል እያለች ለምትጠብቀው
እሱማ ተክቷል ማስታወሻ አለው።
ከሆነ እንግዲህ ጥሪው ከፈጣሪ
ልጆችና ሚስቱን ያፅናቸው ፈጣሪ።
እንግዲህ ምን ይሁን ሞትም ህግ ነው
መላቤተሰቡን እግዚአብሔር ያስበው።
ለቀበና ማህደር መፅሔት ያወጣችሁ
በገንዘብ በጉልበት የተሳተፋችሁ
የቀበና ልጆች በዚህ አጋጣሚ እግዚዘብሔር ይስጣችሁ።

ፀሐፊ፡ ሲ/ር የመንዝወርቅ ተፈራ (ጨኒ)
አቀናባሪ፡ ደመቀ ጀምበሬ

## በጋንፉሬ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ለሐዘን መግለጫ የቀረቡ

### ቆይ ባክህ ጋንፉር

ቆይ ባክህ ጋንፉር
ሰብሳቢያችን አባት ነገር
ባክህ አንዴ እንነጋገር።
በረሃብ፤ በጥም በቁር
በጥይት፤ በቦምብ በሃሩር
　በገደሎች ዝቅታ
　በተራሮች ከፍታ
　ያልተናጋ ያልተረታ
　እንዴት ተሰፋህ፤ በሞቀ ከተማ ተፈታ?
ይህ ግለኝነት፤ ከየት መጣ ከወደኋላ?
ለሃገር፤ ለህዝብ መሞት አልነበረም የአንተ ትውልድ መሃላ?
　አንተ ከሞትህማ
　ያፍሩሱት ያን ከተማ
　ቀበና ኮሪያ ሰፈር፤ እትብትህ ያረፈበትን አውድማ።
ሰብሳቢያችን፤ እባክህ ቆይ
አንድ ቀን እንኳን እንጫወት ቀበና ላይ።

ደገኛው (ከቀበና)

### እሪ በይ ቀበና

እሪ በይ ቀበና፤ እሪ በይ ሰፈሬ፤ ዛሬም እንደገና
ሌላውን ብርቅዬ ፤ ሌላውን ተሚጋች ሸኝተሻልና
　ካንድም ሁለት ሦስቴ የተፈተነልሽ
　ሁሉንም ድል አርጎ አፋፍ ብቅ ያለልሽ
　ያ ደፋሩ ልጅሽ፣ ጋንፉሬ ወዳጅሽ፣ ጋንፉሬ አክባሪሽ
　የሆዱን በሆዱ፣ የልቡን በልቡ፣ እንደቋጠረልሽ
　ቻው እንኳን ሳይልሽ፤ ሳይሰናበትሽ
ቀድመው የሄዱትን ፤ ጥንት የተሸኙትን
ካንቺ የራቁትን፤ እናቱን፣ አባቱን፣ ወንድሙን፣ ጓዶቹን
　ሊጠይቅ ሊጎበኝ ናፍቆቱን ሊናገር
　ከማንም ሳይመክር፤ ለማንም ሳይነግር
ሄደልሽ፤ ራቀልሽ፤ ምሎ ተገዝቶ ድጋሚ ላያይሽ
ጸጥ እረጭ አለልሽ፤ ያ ደፋሩ ልጅሽ
　እሪ በይ ቀበና ፤ አልቅሺ ቀበና ፤ ዛሬም እንደገና
　ድል አድራጊው ጀግና፣
　ድል አድራጊው ልጅሽ፣ እጁን ሰጥቷልና።

ከቆለኛው (December, 2015)

## ለጋንፉሬ የሰማንያ ቀን መታሰብያ የቀረቡ

### እሮሮ

ለወገኖቹ ሚች ላገር ተቆርቋሪ፣
ለሃቅ የቆመ እውነት ተናጋሪ፣
እንግዳ ተቀባይ ቀበናን አክባሪ፣
ነበረ ጋንፉሬ እግዚአብሔርን ፈሪ።
　ለቀበና ልጆች የነበረው ፍቅር፣
　ተዘርዝሮ አያልቅም በደፈናው ይቅር።፣
ጨዋታና ሣቁ ቀልዱና ፈገግታው፣
እንደማር ወለላ የማይጠገብ ነው።
　ማቆሚያ የለውም የጋንፉሬ ታሪክ፣
　በምንም ሁኔታ አያገኝም ምትክ፣
　አለማንሳቱ ነው መንፈስን ከሚያውክ።
ያ ሁሉ ጨዋታ ያ ሁሉ መሯሯጥ፣
እንደዳልጋ አንበሳ ስትቦርቅ ስትሮጥ፣
ብሉልን ጠጡልን እያልክ ስትራወጥ፣
ለካስ ለዚህ ኖሯል ያ ሁሉ መሽቆጥቆጥ።
　ኧረ ለመሆኑ ምንድን ነው ነገሩ፣
　መሠረቱ የት ነው የመነሻው ሥሩ፣
　ምነው ብንረዳው ታሪኩን ባጭሩ፣
　መፍትሄ ያላገኙ በረቂቅ ምስጢሩ፣
　ያቀዳቸው ይቅሩ እንዲህ በጅምሩ?
　ሃሳቡና ቀልዱ ጨዋታው ማማሩ፣
　ያጫወተን ሁሉ መና ሆነው ይቅሩ?
ኧረ ለመሆኑ ኤልሳቤጥ እንዴት ነች?
ከቤቱ ስትጠፋ ምንስ ትልሃለች?
ጆሮዋ እየሰማ ድርጊቱን እያየች፣
መልሱን ካልነገርካት ትፋረድሃለች።
ኧረ ለመሆኑ ምን ይላሉ ሰዎች?
ሁሉን ለመዘርዘር ለወሬም አይመች፣
ለመስጠት አልቻልንም በቂ ምክንያቶች።
　ለጊዜው ተታለህ መስሎ የሚጠቅምህ፣
　እንግዲህ ደህና ሁን ያንን ከመረጥህ፣
　ነፍስህን በሰማይ እግዜር ይማርልህ።

ጌታቸው በላይነህ (ዶ/ር)
አትላንታ ጆርጂያ

### ምንድነው ሚስጥሩ?

ጋንፉር ወንድማችን አብሮ አደጋችን
አትመለስም ወይ በቃ ጨከንክብን
ማንም አልገመተም እንዲህ መሆንህን

አብረኸን አድገህ ሰፈሩን አድምቀህ
ያ የልጅነት ጊዜ ተጫዋችነትህ
ያ የልጅነት ጊዜ ደስተኛነትህ
አሞኝቶን ነበር ስለማንነትህ
ሰርግ እንኩዋን ሲደገስ በሰፈራችን
ዘፈኑም አይደምቅም አንተ ከቀረህ
በእስፖርት ጨዋታው በእስካውትነቱ
የሚያስደንቅ ነበር ተሳትፎህ በእውነቱ
ጊዜው ሲጠይቅም ያንተን ቆራጥነት
ታገለህለት ነበር ለዛ ለደሀ ህዝብ ቀን እንዲወጣለት
ለዛች ኢትዮጵያችን ለሁላችን ሀገር
ለርሃብ ለጥማት ጭራሽ ሳትበገር
ከሰፈርም ለቀህ ከሀገር ተሰደህ
ቆስለህላት ነበር በጣም ተሰቃይተህ
ህይወት ቀጠልክና በዚች ባሜሪካ
አግብተህ ወላልደህ ቤትህ ተሟሙቆ ተላብሰህ በረካ
አሸንፈህ ሁሉን፣ ያንን ሉኪሚያ
ምንድነው ሚስጥሩ ፈልቅቆ ያወጣህ ከቤተሰብ ጉያ
እኛ ቀበኖችን ቀጠሮ አስይዘህ ለስብሰባችን
ሚስጥርህን ይዘህ ሳታወያየን
ምነው ጋንፋራችን እንዲህ አይነት ስራ የሰራህብን
ከሁሉም በላይ የነበረው ፍቅርህ ሰው ወዳድነትህ
አስደንጋጭ ሆነብን ድንገት መለየትህ
ምንኛ ጨክነህ ተለያየሀቸው
እነኝህ ልጆችህ ሦስቱም ባንድ ጊዜ በመመረቂያቸው
እንግዲያው ጨክነህ ከሄድክብንማ ምን እናደርጋለን
እግዚአብሔር ነፍስህን በክበረ ቦታ እንዲያኖራት እንለምናለን።

ከግርማ ታደሰ

## ቀጠሮ

ከረምት ሲገባ ሰማዩ ግም ሲል
ሃገር ቤት ዝናብ ሲጥል
ሌላው ዓለም በሙቀት ሲቃጠል
በነዚያ ውብ ቀናት
የእረፍት ወራት
እንገናኝ ብለህ
አገሩን ሁሉ ቀጥረህ
ልጆችህን በመመረቂያቸው
ቀበኖችን በመገናኛቸው
ላዋቂ ለልጁ
ቀጠሮ ሰጥተህ በየፈርጁ
እንገናኛለን፣ እንደሰታለን ብለህ
የሁሉንም ልብ አንጠልጥለህ፣ አማለህ
ልጆችህ በጉጉት ሲጠብቁ
ቀበኖች ሊያዩህ ሲናፍቁ
የበዓሉ መሪ፣  አቀነባባሪ
የዝግጅቱ ሰሪ፣ ፈጣሪ
ዋናው ሹፌር ሆነህ ሳለህ
የማያምርብህን መርጠህ
ቀጠሮ አክብሩ ባዩ ቀጠሮ አፍርሰህ
ያለቦታህ፣ ያለሰፈርህ ተገኝህ
ጥንትማ ሳለን ቀበና
የዛሬን አያርገውና
ቀጠሮ አክብሩ እያልክ
ተቆጪው አንተ ነበርክ
ያ ቀርቶ ቃልህን አፍርሰህ
ከሌላው ከበለጠው አባትህ
ከዋነኛው ፈጣሪህ
የነበረህን ቀጠሮ ሚስጥር አድርገህ
ሸሽገህ፣ ከሁሉም ደብቀህ
አቅጣጫ ቀየርህ፣ ተሸኘህ
ከአይናችን ተሰውረህ
መመለሻ በሌለው በር ገባህ
እኛም በበኩላችን
ትልቁ ቀጠሮ መፍረሱን
ስናውቀው ቁርጣችንን
እሪ ብለን ጮኸን
ምርር አርገን አልቅሰን
ከዚያም ፀጥ፣ እርጭ ብለን
በየቤታችን፣ በየጓዳችን ተከተን
ብናስበው፣ ብናወጣ ብናወርደው
እንዴት ነው የሚሆነው?
ያላንተ ምርቃቱ
ያላንተ ግንኙነቱ
ብለን ጠየቅን
ከራሳችን ጋር ተሟገትን
እንዴት ነው የሚሆነው ጋንፋሬ?
እስቲ ተጠየቅ ዛሬ
መልሱ መቼም ቀላል ነው
ቃለ አባይ መባሉን ካልፈራኸው
ቀጠሮ አፈረስክ አይደል?
እመን እንጂ፣ ተቀበል
የሁሉንም ልብ መስበርህን
አንጀት ማሳረርህን
እመን እንጂ፣ ጋንፋሬ እመን።

ከቆለኛው (February, 2016)

# ከዚህም ከዚያም

## የኔታ ጥሩነህ

ስመ ጥሩው አባት የኔታ ጥሩነህ እንግዳ በመላው ቀበና የታወቁ ዝነኛ አስተማሪ ነበሩ። የኔታ ጥሩነህ የሚያስተምሩበት ሰፈር ቤላ ኃይለሥላሴ ወይም የቀድሞው የክብር ዘበኛ ካዴት ት/ቤት (ወደ ሐረር ክፍለ ሃገር ከመዛዋወሩ በፊት) ወይም ከምድር ጦር ሆስፒታል በታች የምትገኝ ኖራ የተቃባች ባለ ሁለት ክፍል ቤት ነበረች። ቤቷም እስከ ዛሬ ድረስ ቆማ ትገኛለች። ሁሌም ሲያልቅ አያምርም ነውና ቤቷ በአሁኑ ሰዓት ከት/ቤት ወደ ወፍጮ ቤትነት ተለውጣ ግልጋሎቷን ለሰፈርተኛው ታበረክታለች። (ፎቶውን ይመልከቱ)



የጥንት የጥዋቷ የየኔታ ጥሩነህ ትምህርት ቤት

የኔታ (አለቃ) ጥሩነህ በጊዜው ለነበረው ትውልድ ትልቅ አስተዋፅዖ ያደረጉ አባት (መምህር) ነበሩ። በዚች ጎጆ ት/ቤት ውስጥ ያልተማረ በአካባቢው ካለ ዕድሉ አምልጦታል ማለት ነው። ይህች ት/ቤት ከተራ ወታደር እስከ ጄኔራል፣ ከተራ ሲቪል እስከ ሚኒስቴር ደረጃ አፍርታለች። የኔታ ጥሩነህ ት/ቤት ለመግባት ከፍተኛ ፉክክር ይደረግ ነበር። ትምህርት ሚኒስቴር የኔታ ጥሩነህን በደሞዝ ቀጥሮ ያስተዳድራቸውም ስለነበር ትምህርቱ ከሌሎቹ የቄስ ት/ቤቶች የተለየና የወር ክፍያም አልነበረውም። ድሮ ቄስ ት/ቤት ለመግባት በወር አንድ ብር ይከፈል ነበር።

ትምህርት ቤቱን ከሌላው የሚለየው በመጀመሪያ ፊደል ከተቆጠረ በኋላ በቅደም ተከተል ግዕዝ፣ አቦጊዳ፣ መልዕክተ ዮሐንስ፣ ከንባብ እስከ ዋና ንባብ ከዚያም በኋላ አውደ ፊደልና አውደ ንባብ ይጠናቀቅና ወደ ወንጌል ይገባል። ከዚያም ከወንጌል ቁጥር እስከ ዋና ንባብ ይገባል። ዳዊት ከመገባቱ በፊትም መዝሙረ ፊደልና አቡነ ፔጥሮስ ስለሚሰጥ እዚህ ላይ የደረሰ ተማሪ የማንበብ ችሎታው የላቀ ይሆናል። ተማሪው ጎበዝ ከሆነ ደግሞ በቀጥታ ዳዊት ሳይማር ወደ አንደኛ ደረጃ ተመላላሽ ት/ቤት በየኔታ አማካኝነት ይገባል። ዳዊት መማር የሚሻ ደግሞ ከሁለቱ (ትምህርቶች) ንባቦች በኃላ ወደ ዳዊት ይዛወራል።

በመሠረቱ ብዙዎቹ የኮከበ ጽባሕ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ት/ቤት ተማሪዎች በየኔታ ጥሩነህ አማካኝነት የገቡ ናቸው። ሌላው ደግሞ፣ የክብረ በዓል ዕለት ወይም የአንድ ሃገር መሪ ለጉብኝት በሚመጣበት ጊዜ (ለምሳሌ ማርሻል ቲቶ የዩጎዝላቪያ መሪና ሌሎችም) ትንንሽ ባንዲራዎች አስይዘውን "አበባ ይዘን ተሸልመን ሠላምታ እንስጠው ለአዲስ ዘመን" የሚለውን መዝሙር እየዘመርን ስድስት ኪሎ ድረስ ተሰልፈን በመሄድ እንግዳውን በክበረና በደመቀ ሁኔታ እንቀበል ነበር።

ይህ ሁሉ ሥርዓት ለወደፊቱ በትምህርታችን እንድንቀጥል የሚያነቃቃን ነበር። በተለይም የቀ/ኃ/ሥ ት/ቤት ተማሪዎች ለምሳና ለዕረፍት ት/ቤት ውለው በየኔታ በር ላይ ትልልቅ መጻሕፍት ተሸክመው ሲመላለሱ ስናይ እኛም አንድ ቀን እነሱ የያዙትን መጻሕፍት ይዘን እንመላለሳለን የሚል ምኞትና ሃሳብ ነበረን።

የኔታ (አለቃ) ጥሩነህ ለትምህርት ያደረጉት አስተዋፅዖ ይህ ነው አይባልም። ከዚህም በላይ ወንድማቸውም አቶ አገኘሁ እንግዳ የመጀመሪያውንና የጥንቱን ሰፊ ወረቀት ላይ የተሳለውን የኢትዮጵያ መንግስት ብር በፊቱ የአፄ ኃይለ ሥላሴን ምስል ከጀርባው ደግሞ ባንዲራውን በመስቀል ላይ ተሸክሞ ያለውን የአንበሳ ምስል ስለው ያበረከቱ አባት ናቸው። አቶ አገኘሁ እንግዳ ታሪክና ምሳሌ ሦስተኛ መጽሐፍ ላይ እንደ "ሁለት አፍ ያሉት ወፍ"፣ "የሸክላ ድስት" እና ሌሎችንም በሥዕል የተደገፉ ጽሁፎችን አበርክተዋል።

በአጠቃላይ የኔታ ጥሩነህ እንግዳ ብዙ ሊቃውንቶችንና መኳንንቶችን አፍርተው ሄደዋል። እስካሁን ታሪካቸው ተጽፎ ለንባብ ባይበቃም፤ ተማሪዎቻቸው ምስክርነታችንን እንሰጣለን።

ዶ/ር ጌታቸዉ በላይነህ
አቶ ሙሉነህ ለገሠ

## የአቡነ ገበረ መንፈስ ቅዱስ መረዳጃ እድር

ሠፈራችን ኮርያ ሠፈር የተባለው፣ አባቶቻችን በተባበሩት መንግስታት ስር የኢትዮጵያን መንግስትና ሕዝብ ወክለው ወደ ደቡብ ኮርያ እየዘመቱ ከተመለሱ በኋላ ነበር። የዘመቱትም በንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ጦር ስር ነበር። ለዚህም ዘማች ጦር ቃኘው በኮሪያ የሚል የዘመቻ ስም ተሰጥቶት ነበር። በሠፈራችን ቅድመ




የደቡብ ኮርያ ከፍተኛ የጀግና ሊሻን ተሸላሚዎቹ አባቶቻችን ከደቡብ ኮርያ ባለስልጣናት ጋር

ኮርያ ዘመቻ ብዙ ሰፋሪም አልነበረበትም ይባላል። ጭሰኝነትም የተጀመረው ይኸው ከኮርያ ዘመቻ እየተመለሰ በሠፈራችን የሚሰፍረው ዘማች ቁጥር አየጨመረ በመምጣቱ ነበር። እንደውም ሦስተኛ ቃኘው ሲመለሱ እንደሆነ ያረጋግጣሉ። በነገራችን ላይ የደቡብ ኮርያ መንግስት በአዲስ አበባ ትልቅ ሆስፒታል አሰርቶ አባቶቻችንን ከእነ ባለቤቶቻቸው ሙሉ ነጻ ህክምና እንዲያአገኙ እያደረገ ነው። ለዘማች ቤተሰብም ልጆቻቸውን ነጻ ትምህርት ሰጥተው በዚህም ብዙዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ለልጅ ልጆቻቸውም ደቡብ ኮርያን ለአንድ ሳምንት እንዲጎበኙ ባዘጋጁት መሰረት በአያቶቻቸው ተጋድሎ ተዝናንተው ከተመለሱት መሃል የኔ ልጅ ይገኝበታል። ስለ ኮርያ አንድ ነገር ልጨምርላችሁና ወደ ሠፈራችን እድር ታሪክ እወስዳችኋለሁ። የደቡብ ኮርያ መንግስት ፷ኛ የነጻነት በዓላቸውን በከፍተኛ ስነ ሥርዓት ሲያከብሩ ከቃኘው ዘማቾች 20 ሰዎችን ጋብዘው በዚያን ጊዜ በተባበሩት መንግስታት ስር ከዘመቱት የዓለም ሰራዊት ጋር አቀላቅለዋቸዋል። የአገሩን ከፈተኛ የጀግና ሊሻን ተሸልመው በክብር ተመልሰዋል። ይህን እድል ካገኙት መሃልም አባታችን የጀ አለቃ ጀምበሬ ደለለኝ ይገኙበታል።

ስለ ሠፈራችን ትንሽ ላውራችሁ ብዬ እንጂ ስለ ኮርያ ዘመቻ መነጋገር ዛሬ ርእሴ አይደለም። እንግዲህ አባቶቻችን በጭሰኝነት መሬት እየተመሩ ሲሠፍሩ አብዛኛውን መሬት በጊዜው ይዘው በባላባትነት የሚያስተዳድሩት ልጅ አርጋው ጳውሎስና ወ/ሮ አምሳለ ነበሩ። በዘመኑ ይደረግ ነበር እንደሚባለው በታሪክም እንደምንሰማው ከነበሩት ባላባቶች በሰፋሪው ላይ የነበረ ግፍና ጭቆና አልነበረም። ተደርጎ ቢሆን እንኳ እኔ የማላውቀው ነው። ልጆቻቸውም ከኛ ጋር በመንግስት ት/ቤት ይማሩ ነበር። እናም እንደገና ወደ ሰፈራው ልመልሳችሁና እስከ አራተኛ ቃኘው መልስ ድረስ ቦታው በሰፋሪ መጣበብ ብቻ ሳይሆን ተጨናንቋል። ይልቁንም በአካባቢው የሚሰሩ የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች፤ ለምሳሌም ከሚኒሊክ፣ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ ከክብር ዘበኛ ሆስፒታሎች ፤ እንዲሁም ከትምህርት፣ ከጡረታ፣ ከገንዘብ ሚንስትሮችና በአካባቢው ከነበሩ ተቋሞች ውስጥ ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩ ብዙ ሰዎች ይህንኑ ሰፈራ ተቀላቅለው በጭሰኝነት ሰፍረዋል። በነበረው ንቃተ ህሊና በወጉ ለመንገድና ሌሎች ጉዳዮች ተገቢው ትኩረት ከጭሰኛውም ሆነ ከባላባቱ ወገን ባለመደረጉ ትውልድን አልፎ ዛሬም በአስቸጋሪ ሁኔታ ኑሮውን እየገፋ ይገኛል። በዛ ዘመን ቤቶች የሚሰሩት እንደ ገጠር ቤቶች ሁሉ ጣሪያቸው በሳር ነበር የሚከደነው። ብዙ ጊዜም በእሳት አደጋ ምክንያት ኡኡታውና እሪታው ይቀልጥ ነበር። ሕዝቡም የዛፍ ቅርንጫፍ እየቆረጠ እሳቱን በመደብደብ ያጠፋ ነበር። የሰውን ፍቅርና ሕብረት ለመግለጽ የኔ ብዕር አቅም የለውም። መቸም እንደምትገነዘቡት ውሃ በጣም ችግር ስለነበር ከየቤቱ የምትገኘው ከማዕድ ቤት ሥራ የተረፈ ካለ ነበር። እናቶቻችን ውሃ የሚቀዱት ከቀበና ወንዝ አጠገብ ካለ ምንጭ ነበር። ወደ እየቤታቸውም የሚያጓጉዙት በእንስራ ሞልተው በጀርባቸው አዝለው የቀበናን ዳገት አቃስተው ነበር። እናቶቻችን እኛን በዚህ ውሃ ምግብ አብስለው፤ ልብሶቻችንንና እኛን አጥበው እንዴት እንዳሳደጉን ስንቶቻችን እናስበው ይሆን? በኋላ በኋላ ግን መንግስት ቦኖ የሚባል በየሠፈሩ ማእከል የውሃ መስመር ዘረጋ።

ደረሰኝ የሚቆርጥ ሠራተኛ ቀጥሮ ያስተዳድረው ነበር። ክፍያውም ለአምስት እንስራ ውሃ አምስት ሣንቲም ነበር። አሁን አሁን ሁሉም በየደጁ ተጠቃሚ ሆኗል። ስለ ቀበናዬ የልጅነት ትውስታዬን ይህን ያህል ከነገርኳችሁ ደግሞ እስቲ ስለ እድሩ ላውራላችሁ። ነገር ግን ይህን ካነበባችሁልኝ በሌላ ርዕስ እንደምመለስ ቃል እገባለሁ። ስለ ቀበናዬ !

ዘመኑ 1947 ዓ.ም ጥር ሰባት ቀን አንድ ነገር ይከሰታል። ትዳርም ሆነ አጋዥ ያልነበራቸው አቅመ ደካማ የነበሩ ወይዘሮ ያይኔ ሊቅ የሚባሉ እናት በጠናባቸው ህመም ከዚህ ዓለም በሞት ያርፋሉ። ለዚህም ጉዳይ የአካባቢው ሠፈረተኛ አስር አስር ብር ከየቤቱ አዋጥተው ማስቀበሪያ ሳጥን ገዝተው፣ ለቀብር ሥረዓቱ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አድርገው መልካም አሸኛኘት ያደርጉላቸዋል። ከዚህም ቀብር ተመልሰው መወያየት ይጀምራሉ። ለምን እድር አንመሠርትም ብለው። በዛው ሰዎች ይመርጡና ሕዝቡን ለስብሰባ እንዲጠሩ ይደረጋል። በእዛው ስብሰባ ዳኛ፣ ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ ገንዘብ ሰብሳቢ እንዲሁም አባላትን ይመርጣሉ። ሥብሰባቸው በየወሩ እንዲሆንና መዋጮውም በየወሩ ሃያ አምስት ሳንቲም እንዲሆን ይወስናሉ። ነገር ግን በየወሩ አከታታይ ስብሰባዎችን አድርገው ለእድሩ መተዳደሪያ ደንብና ሥርአት አርቀው፣ እያንዳንዱንም አባል አስፈርመው ከጨረሱ በኋላ በ1948 ዓ.ም አዲስ መሪዎችን መረጡ። እድሩንም በህጉ መሠረት ማስተዳደር



ጀመሩ። እነርሱም የሥራ ድርሻቸው ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

1ኛ. ዳኛ 2ኛ. ፀሐፊ 3ኛ ገንዘብ ያዥ 4ኛ. ሂሣብ ተቆጣጣሪ እንዲሁም አምስት አባላት እንዲኖሩት ህጉ ስለሚደነግግ በዚሁ መሠረት ነበር ተመርጠው ወደ ሥራ የገቡት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው የእድሩ ዳኞች ከነበሩት መሃከል እኔ የማስታውሳቸው ፶ አለቃ ብርሃኑ አደላ፣ ባላንበራስ ጥላሁን ወልደማርም፣ ፻ አለቃ ጀምበሬ ደለለኝ፣ ፻ አለቃ ፍስሃ፣ ኮሎኔል አሰፋ ወልደየስ፣ አቶ ታምሩ፣ አሁን ደግሞ ኮሎኔል አበራ ኪቲላ ይገኙባቸዋል። ከጊዜ ብዛት ስማቸውን የዘነጋኋቸው ብዙ ናቸው።

ከህጎቻቸውም መሃከል ማንኛውም ሰው ከስድስት ወራት ያህል በሠፈሩ ውስጥ ነዋሪ ከሆነ፥ ወደ እድር አባልነት እንዲገባ በአባላቱና በኮሚቴው በተደጋጋሚ ይጋብዙታል። ነገር ግን በእድሩ ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ካልሆነ፥ በሃዘኑ ወይም በደስታው ከጎኑ የሚቆም ማንም አይኖርም። በድንገተኛ አደጋውም የሚደርስለት የለም።

በጉርብትናም ሆነ በሌላ ግንኙነት ሲረዳው የተገኘ እድርተኛ ከተገኘ እድሩ በሕጉ መሰረት የቅጣት እርምጃ ይወስዳል። ስለዚህም ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍል እድረተኛ ወይም የእድር አባል ይሆናል። በችግረኛነቱ የሚታወቅ ማንም ሰው በራሱም ሆነ በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ ቢደርስበት ለቀብር ሥርአት የሚያስፈልገውንና ሳጥን ገዝተው ይሸኙታል። ምንም እንኳን ሰፈራችን ወታደር ቢበዛውም ዘመቻን ወይም ሹመትን ወይም ምርቃትንና የመሳሰሉትን ሁሉ በተመለከተ የተዘጋጀ ህግ የለም። በችግረኝነትም በጤና ችግር ምክንያት ለህክምና የረዱት ሰው የለም። ህጉም ድጋፍ አያደርግም። አይ የኔ ነገር! መጀመሪያ መነገር የሚገባውን ታሪክ ወደመጨረሻ ወሰድኩባችሁ። እድሩ ሲቋቋም አንዱ አጨቃጫቂ የነበርው ጉዳይ ስሙ ማን ተብሎ ይጠራ የሚለው ነበረ። ግማሹ "ኮርያ ሠፈር መረዳጃ" ሲል ገሚሱ ደግሞ በባላባቱ "ነጋድራስ ጳውሎስ መረዳጃ"፣ ሌላውም ሌላ እያለ ተሟገቱ። ነገር ግን እኛ ወታደሮች ሆነን እድራችንን ወታደር አናደርገውም ደግሞም እኛ ጭሰኞች ሆነን እድሩንም በጭሰኝነት አናስመራውም ብለው ኃይለኛ ሙግት የገጠሙት አሸነፉና በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ስም እንዲጠራ ተወስኖ "የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መረዳጃ" ተብሎ ተሰየመ። ከጊዜ በኋላ መንግስት ማህበራትን ማደራጃ ብሎ ባወጣው አዲስ መግለጫ መሰረት ለተወሰኑ ዓመታት "የነገድረስ ጳውሎስ ሠፈር እድር" ተብሎም ነበር። ነገር ግን ደግሞ በሌላ የመንግስት መግለጫ ወደ መጀመሪያ ስሙ እንዲመለስ ተደረገ።

እድሩ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ የገጠመው ከፍተኛ ችግር የራሱ የሆነ ለአባላቱ መሰብሰቢያና ንብረቶቹን ማስቀመጫ ቦታ አለማግኘቱ ነው። አሁንም ችግሩ እንደቀጠለ ነው። እኛም በደስታም ሆነ በሐዘን ወንበርና ጠረጴዛ በየቤቱ በማጓጓዝ ስንረዳ ነው ያደግነው።

ከዚህ ጽሑፍ ጋር ካያያዝኩት አንዱ ፎቶግራፍ አባቶቻችን እድሩን አቋቁመው ከጨረሱ በኋላ ለመታሰቢያነት የተነሱት ፎቶ ነው። የገረመኝና ቀልቤን የወሰደው ግን በፎቶው ጀርባ ላይ ተጽፎ ያነበብኩት ነው። "የእድሩን መቋቋም ምክንያት በማድረግ ለልጅ አርጋው ጳውሎስ በመታሰቢየነት ተሰጠ" ይላል።

በፎቶው ላይ ሳርያን ቅድ ለብሰው መጋዝ ወይም መሳሪያ የያዙትን የሚያውቃቸው ሰው አላገኘሁም። ስለዚህም ካስፈለገ ለአፋልጉኝ እናመለክታለን። መሃል የሚታዩት ለብዙ ጊዜ ከመጀመረያ ምርጫ ጀምሮ በዳኝነት፣ በጣም በተወዳጅነት ሕዝቡን ሲያገለግሉ ነበሩ። የሁሉንም ማእረግ ያደረግሁት ሥራቸውን ሲያቆሙ በነበረበት ነው።

1) ስማቸው አልታወቀም
2) የ ፶ አለቃ ድረሴ ወ/ዮሐንስ (አባል)
3) የ ፻ አለቃ የማነ ተመስገን (ገንዘብ ሰብሳቢ)
4) የ ፲ አለቃ እሸቴ ወ/ማርያም (አብዬ፣ አባል)
5) አለቃ ብርሃኑ አደላ (ዳኛ)
6) የ ፶ አለቃ ወርቁ ተሰማ (አባል)
7) የ ፻ አለቃ ጀምበሬ ደለለኝ (ፀሐፊ)
8) ባላንበራስ ጥላሁን ወ/ማርያም (አባል)
9) አለቃ ገብሬ
10) የ ፲ አለቃ ወንድሙ አረዶ (ንብረት ያዥ)

ከዚህም በኋላ ብዙዎች አባቶቻችን በየጊዜው በተደረጉ ምርጫዎች እየገቡ አገልግለዋል። ከነዚህም መሃከል የ፶ አለቃ ተፈራ ኃይሌ፣ አለቃ አየለ እንየው፣ ሻንበል ባሻ ደስታ ዴንሳ፣ ፶ አለቃ ኃይለ ማርያም ክፍሌ፣ ፶ አለቃ ተፈራ እርገጤ፣ አቶ መለሰ ባዬ፣ ፲ አለቃ ተክሉ ውድነህ፣ ፲ አለቃ ተክለማርያም ከማስታውሳቸው ጥቂቶቹ ናቸው። እድሩም ባለፈው ዓመት 60ኛ ዓመቱን በታላቅ ስነሥርአት አክብሯል። በበዓሉ ላይ ተወካይ እንድትልኩ ስላልተጋበዛችሁ፣ እኔም ስላላሳሰብሁ በእድሩ ሰም ይቅርታ መጠየቅ ይገባኛል። የአሁኑ አመራር በየዓመቱ በሚከበሩት መንፈሳዊ በዓላትም በሰፈሩ የታወቁ አቅመ ደካሞችን፣ ችግረኞችን በፋሲካ፣ በገናና እንዲሁም ለአዲስ ዓመት በዓሉን ተደስተው እንዲያሳልፉ ያደርጋሉ።ይኸም ግለሰቦችን በማስተባበር ነው። ረጅዎችንም፣ አሰረጅዎችንም በአካባቢው ስም እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። እናንተም ሰላም ሁኑልኝ!

ደመቀ ጀምበሬ

# የቀበና ትዝታ




የዛሬው የህብረት ፍሬ ትምህርት ቤት

## እነማን ነበሩ

ውድ አንባቢያን ሆይ ይህን ርዕስ ለመጠቀም የጓጓሁት አበው ሲተርቱ “ነገርን ከስሩ ውሀን ከጥሩ” ይሉ ነበር። አባባላቸው ቁልጭ ያለ ትርጉም ያለው ነው። እኛም ስለ ቀበና አመሠራረት ማወቅ ስላለብን ከየት እንደ ተነሳና ካለንበት ዘመን እንዴት እንደ ደረሰ በቅደም ተከተል ከአባቶቻችን የሰማሁትን በጽሑፍ ማቅረብ ስላለብኝ ይህን ርዕስ ተጠቅሜበታለሁ። ምንም እንኳን ቀበና ስትቆረቆር እኔ ባልወለድም፣ በሰበሰብኩት መረጃ መሠረት ያለኝን ላቋድሳችሁ ወሰንኩኝ። ባለማወቅ የተዘለለ ወይም የተረሳም ካለ የተሻለ ሃሳብና እውቀት ያላችሁ አንባቢያን ብታብራሩና ብትጨምሩበት ደስ ይለኛል።

የቀድሞ ስሟ ፊንፊኔ በኋላም ደግሞ በእቴጌ ጣይቱ ስሟ ተቀይሮ አዲስ አበባ በመባል የምትጠራው የመናገሻ ከተማችን የተቆረቆረችው በዝነኛው ንጉሥና የአድዋው ጀግና በአፄ ምኒሊክ ጊዜ ነበር። በዘመኑ በአገዛዙ ሥር የነበሩት ባለሙያዎች ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ከተማዋን በንጉሡ ፈቃድ ለማስፋፋት እንዴት ገጠሩን እየመነጠሩ ከተማ ለመከተም ተከፋፍለው እንደሰፈሩ ለመግለጽ እሞክራለሁ። በቅድሚያ ወደ እኛ አካባቢ ልመለስና የሰማሁትንና ያየሁትን ወይም የማውቀውን አቀርባለሁ። የላይ ሠፈር፣ የታች ሠፈር፤ የማዶ ሠፈር በማለት በቅደም ተከተል ባስቀምጠው ለጽሑፌ መልክ ይሰጠዋል ብዬ አምናለሁ።

የላይኛው ሠፈር ማለት የክብር ዘበኛ ቲያትር ያሳዩበት ከነበረው ቦታ አንስቶ እስከ ወታደሮች ካምፕ ድረስ የደጃዝማች መሸሻ ግቢ

ሲባል፤ በኋላ ክብር ዘበኛ አጠቃሎ ወስዶታል። በምትኩም ለልጃቸው ለደጃዝማች ዳምጠው የሚኖሩበትንና የጋራ ኋላ እንዲሁም ሸክላ ሜዳን ጨምሮ በስራቸው ተቆጣጥረዋል። በነዚህም ሠፈሮች ብዙ ጭሠኞችን መርተዋል።

በመካከለኛው ሠፈር ደግሞ የሊቀ መኳስ አጥናፍ ሰገድ ሠፈር ሲባል አፄ ምኒልክ ለእኚህ ታላቅ አባት ይህን ቦታ ሰጥተዋቸዋል። እኚህ አባት በአፄ ምኒልክ በጣም የተወደዱ እንደነበሩ አበው ይናገራሉ። እንዲያውም ንጉሱ እስከ ቤታቸው ድረስ ይመጡ ነበር ይባላል። እኚህ አባት ከማንም የበለጠ ብዙ ልጆች አፍርተዋል። በኋላም ልጆቻቸው የሀገሪቱ ዋና ዋና ባለስልጣኖች ሆነው ነበር። እኔም ደርሼ ከልጆቻቸው መካከል ጥቂቶቹን ለማየት በቅቻለሁ። ለአብነት ያህልም ፊትአውራሪ ሀይሌ፣ አቶ አለማየሁና ወ/ሮ ጥሩወርቅ ሲሆኑ፤ ያላየኋቸው ደግሞ ፊትአውራሪ አበበ፣ ፊትአውራሪ ደስታ፣ ፊትአውራሪ ዘውዴ ሲሆኑ ስማቸውንም ያልጠቀስኩት ይኖራሉ። የልጅ ልጆቻቸውም ጀኔራሎች፣ እንደራሴዎች፣ የዘውድ አማካሪዎች በመሆን እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ ነበሩ።

ሊቀ መኳስ አጥናፍ ሰገድ ለቀበና እድገት ያደረጉትን አስተዋጽዖና ውለታ ለማስታወስ በቀበና የመጀመርያውና አንጋፋው የመረዳጃ ዕድር ሲቋቋም የዕድሩ መጠርያ ስም "ሊቀ መኳስ አጥናፍ ሰገድ" እንዲሆን አባላቶቹ ወሰኑ። ይህ የመረዳጃ ዕድር ሲቋቋም መንደርተኛውን ያሰባሰቡት፣ ድንኳኑን ያሰፋትና የዕድሩን የመጠሪያ ስም ሃሳብም ያቀረቡት የኔ አባት ነበሩ። በጊዜው ልጆችም ቢሆኑ እነ አባባ ተበጀ፣ ወ/ማሪያም ሰይፋና መኮንን አክሌ ያገለግሉ እንደነበር ሰምቻለሁ። የዕድርተኛውም ቁጥር አነስተኛ ነበረ ከ 25 እስከ 30 ይደርስ ነበረ)። ዕድሩ ሲቋቋምም የወር ክፍያው ሃምሳ ሳንቲም ብቻ ነበረ። በኋላ ግን የአባላት ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ የወር ክፍያው ወደ አንድ ብር ከፍ ብሎ ነበር። ከጥቂት ዓመታትም በኋላ የመረዳጃ ዕድር ጠቀሜታው እየታወቀ ሲመጣ፤ ከባቡር መንገድ፣ ከቆርቆሮ ሠፈርና ከአቶ ዳኜ ግቢ መጥተው ቤት የሰሩ ሰዎች በመሰባሰብ የነጋድራስ ጳውሎስን ዕድር አቋቋሙ። ከዚያም በኋላ የህዝቡ ቁጥር በየአቅጣጫው እየጨመረ ሲመጣ ዕድርም እንዲሁ በየአካባቢው እየተስፋፋ መጣ።

ሌላው ደግሞ ከቀድሞው ቆርቆሮ ሰፈር በታች ከሬሳ ቤት በመለስ እስከ ሾላው ድረስ የደጃዝማች ገድሌ ሰፈር ተብሎ ሲጠራ ውሃ አየጠጣን ያደግንባት "የሾላ ውሃ" የምንላት የደጃዝማች ገድሌ ምንጭ ትባል ነበር። ደጃዝማች ገድሌ ብዙ አርበኞችና ሀገር ወዳድ ልጆች አፍርተው ያለፉበት ሠፈር ነው። ከቅርብ አገልጋዮቻቸውም መካከል አቶ አረሩ ገድሌን ማስታወስ ይቻላል። እንዲሁም አባባ (አቶ) ዳኜ ወይም የቅጽል ስማቸው "አባ ሰበር" የሚባሉ ቀበናን የቆረቆሩና ነበሩ። አባባ ዳኜ ዕድሜአቸው በጊዜው 120 የነበረ ሲሆን ግቢያቸው ከአቶ ለገሠ ወልደ ሰንበት ወይም ከአቶ ተካልኝ ታዬ ባሻገር በአንድ በኩል ከክቡር ዘበኛ ካምፕ ጋር ወይም ትግሬ ግቢ (የቀድሞ ቆርቆሮ ሠፈር) ተብሎ ከሚጠራው ጋር የሚዋሰን ነበር። የአባባ ዳኜን ኮክና ወይን እንዲሁም የቀኝ አዝማች ማርቆስን ወይን ያልቀመሰ ወጣት አልነበረም።

በተለይም በእኔ ዕድሜ ክልል የነበረን፤ የማንንም ስም ሳላነሳ፤ የአባባ ዳኜን ግቢ ሳይጋበዝ ያልገባኝ የለም። ግቢው በቁልቋልና በሰንሰል የታጠረ ቢሆንም ለመግባት አስቸጋሪ አልነበረም። የተቻለው ኮኩን ሌላው ደግሞ ወይኑን ሲያወርድ አባ ሰበረ የሚከላከሉት በወንጭፍ ብቻ ነበር። በጎም ቢሆን መጥፎ የልጅነት ሥራ አይዘነጋም።

በእዚሁ አካባቢ ከዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል በስተጀርባ ሌላ ግለሰብ ይኖሩ ነበር። ስማቸውም አቶ ሣላ ይባሉ ነበር። ለአቶ ሣላ አፄ ሚኒልክ ከሆስፒታሉ በስተጀርባ ቦታ ሰጥተዋቸው ቤት ሰርተው ልጆች አፍርተው እንደነበሩ እኔም አውቃለሁ። ከአቶ ሣለ ቤት ወረድ ብሎ ሌላ የታወቁ አባት ነበሩ። ስማቸውም ነጋድራስ ጳውሎስ ይባላል። የሠፈሩም ስም "ነጋድራስ ጳውሎስ ሠፈር" በመባል ይጠራ ነበር። ከነጋድረስ ጳውሎስ በታች ከዱቤ ባሕር አጠገብ ቀኝአዝማች ፈረደ የሚባሉ ነበሩ። ከቀበና ማዶ ወይም ከዕድር (ሣህለ ሥላሴ) ት/ቤት ባሻገር መነዕር ከምትባለው መዋኛ ባሕር አንስቶ እስከ ቤላ ድረስ የደጃዝማች ክፈተው ሠፈር ሲባል ልክ እንደ ደጃዝማች ገድሌ ምንጭ (የሾላ ውሃ) በስማቸው "የደጃዝማች ክፈተው ምንጭ" የምትባል ከጀርመን ኤምባሲ አጥር ሥር እንደነበረች አስታውሳለሁ።

ቀበና ብዙ ጀግኖች አባቶችና እናቶችን ያፈራች ሠፈር ነች። እነ ብላታ አፈንጉሥ፣ በኋላም ደጃዝማች ኃይሌን፣ ቀኝአዝማች ደሀኔን የመሳሰሉ አባቶች ያበረከተች ነች። ሌላው ደግሞ ከዕድር ት/ቤት አንስቶ እስከ ደረቁ ድልድይ በላይ ድረስ ያለው የደጃዝማች ገ/ሥላሴ ጫካ ተብሎ ሲጠራ የደጃዝማቹ ማረፊያ ቤት በዘመናዊ መልክ የተሰራ ቪላ ነበር። እስካሁንም ቆሞ ይገኛል። ከእዚህም ከፍ ብሎ የአማቻቸው የልውል ራስ ሥዩም ቤት ሲሆን ቀጥሎም እስከ ፈረንሳይ ሌጋሲዮን ድረስ ያለው የአፈ ንጉሥ ጥላሁን ሠፈር እየተባለ ይጠራ ነበር።

እንግዲህ በተቻለ መጠን አቅሜ የፈቀደውን ያህል የታሪኩን አንኳር በመዘርዘር በሕይወት ከነበሩት አባቶች የሰማሁትንና በልጅነቴም ያየሁትን የሰፈሩ ቆርቋሪዎች ስላደረጉት አስተዋፅዎ ለእኛና ከእኛ በኋላ ለመጡት እንዲሁም ለሚመጡት ትውልዶች ያስተላለፉትን ታሪክ ማወቁ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት ብዙ ሐተታ ውስጥ ሳልገባ በመጠኑ ቋጭቼዋለሁ። ከዚህ የተለየ ያልተጠቀሰ ከተገኘ በቀጣዩ መጽሔት ላይ እናወጣዋለን። በመጨረሻም ለማሳሰብ ያህል ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከውዲቷ ባለቤታቸው ከቴጌ ጣይቱ ጋር አዲስ አበባን (ፊንፊኔን) ሲቆረቁሩ እነኚህ አባቶችና መኳንንቶች ከንጉሡ በተሰጣቸው ሐላፊነት ዱሩን በመመንጠርና በማሳመን ጦር ሠፈሩን (ከተማውን) ከትመዋል።

ዶ/ር ጌታቸው በላይነህ

# ቀበናዬ ዞሮ መግቢያዬ

እስቲ እኔም እንደ ቀበናነቴ ወግ ይድረሰኝ ብዬ፣ ደግሞም ዝም ብዬ ላልፈው ያልቻልኩት አሳዛኝ አጋጣሚ በመምጣቱ ተደፋፈርኩ እንጂ የስነ ፅሑፍ ችሎታ እንኳን አሁን በወጣትነት ዘመኔም አልነበረኝም። ነገር ግን የምጽፈው ለቀበኖቹ በመሆኑ የቤተሰብ ውይይት ስለሚሆን ተጽናንቻለሁ።



የ፻ አለቃ ጀምበሬ ደለለኝ በወጣቶች ቀን ላይ ንግግር ሲያደርጉ

ይህን ፎቶግራፍ መነሻ አድርጌ የልጅነት ሕይወታችንን በጥቂቱ ልተርክላችሁ ተነስቻለሁ።

ከጊዜ በኃላ ቃኘው በኮርያ ተብሎ ይጠራ የነበረ በሠፈራችን ወጣቶች የተቋቋመ ማህበር ነበር። ነገር ግን ለዚህ ማህበር መቋቋም ምክንያት የነበረው አበሮ አደጎቹ ሐኪም ሜዳ እየተባለ ይጠራ በነበረው ሰፊ ቦታ ላይ የእስፖርት እንቅስቃሴዎችን እናደርግ ስለነበረ ነው። በዚሁ ሐኪም ሜዳ ወደ ኋላ ላይ ተደራጅተን የአቡዋሬ አካባቢ ወጣቶችን እንዲሁም እስከ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ድረስ ያሉ ወጣቶችን እየጋበዝን ዋንጫ ገዝተን የእግር ኳስ ጨዋታ ውድድር እናደርግ ነበር። በዚህም አላበቃን በየዓመቱ የወጣቶች ቀን ብለን ወላጆቻችንን በሙሉ በመጋበዝ የእግር ኳስ ግጥሚያ ከሌላ ሰፈር ወጣቶች ጋር፣ የተለያዩ የእሩጫ ውድድሮች፣ የአክሮባት እንቅስቃሴዎችን እናደርግ ነበር። ጊዜውም ጥሩ ስለነበር ወላጆቻችንም በጣም በሞራል ያግዙን ነበር። በተለይም በማስታወቂያ ሥራ ተሰማርቶ የነበረው አቶ ወንድሙና የ፶ አለቃ ገብረሥላሴ በገንዘብም ከሚረዱን ዋናዎቹ ነበሩ። መቸም አምስት ብር የሚሰጠን ካገኘን የሠፈሩ ንጉሥ አድርገን ነበር የምንወስደው። የእስፖርት ማሊያችንንም በዚሁ በወጣቶች ቀን በሰበሰብነው ገንዘብ እንገዛ ነበር። ለአስራ አንድ ተጫዋቾች ከ12 እስከ 15 ብር በማዋጣት ሙሉ ትጥቅ ጫማና ገንባሌ ሲቀረው ይገዛልን ነበር። አይ ጊዜ!

ወይ ጉድ ልጽፍላችሁ የተነሳሁበትን ትቼ ልቤ ብክን ብሎ ሌላ ጨዋታ ውስጥ ይዣችሁ ልገባ ነበር። እስቲ ወደ ተነሳሁበት ጽሁፌ ልመልሳችሁ። ከላይ በፎቶው የምታዩዋቸው አባታችን የ፻ አለቃ ጀምበሬ ደለለኝ ናቸው። ንግግር የሚያደርጉትም በዚሁ በወጣቶች ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መረዳጃ እድርን ወክለው ነበር። ቦታውም እኛ በጊዜው የእድር ትምህርት ቤት ብለን የምንጠራው የትምህርት ክፍሎች ኮሪዶር ወይም በረንዳ ላይ ነበር። የሰፈራችንም ወጣቶች አደግ ስንል በዚሁ የእድር ትምህርት ቤት ኳስ ጨዋታችንም ውሎአችንም በዚያ ሆኖ ነበረ። አባቶቻችንም ይህን ት/ቤት በንጉሱ ዘመን እንዴት ተደራጅተው እንደሰሩት የኛንም በቦታው ላይ የነበረንን የልጅነት ትዝታዎች ወደፊት እጽፍላችኋለሁ። እንደገና ወደተነሳሁበት ልመልሳችሁና በእድር ት/ቤት ወላጆቻችንን መሰብሰብ ያስፈለገንም ማህበራችን እያደገ በመምጣቱ ለሕብረተ ሰቡም የምንሰጠው አገልግሎት እየተወደደልን በመምጣቱ፤ እኛም መድረክ አዘጋጅተን ብዙ እንግዶችን ስለምንጋብዝ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ስለተገኘ ነበር።

በፎቶ ግራፉ ላይ ከአባታችን ቀጥሎ የሚታየው ወጣት ፍቃዱ ሣህለድንግል፣ የሰፈር ቅጽል ስሙም (ቢሉ) ይባል ነበር። የእኛን የወጣት ማሕበር ለማስተባበር ብዙ ይደክም ነበር። በእስፖርቱም ዘርፍ እንደ ሌሎቻችን በሁሉም ዓይነት እስፖርት ሁለ ገብ ባይሆንም ጊዜው እነ ሻምበል አበበ ቢቂላ ሮምና ቶኪዮ አገራችንን ወክለው በኦሎምፒክ ማራቶን እሩጫ ያሸነፉበት ዘመን ስለነበር፤ ፍቄም በዚሁ የማራቶን እሩጫ ፍቅር ተነድፎ ለረጅም አመታት ሲሮጥ ነበር። በሠፈራችንም በማራቶን እሩጫ ተወዳዳሪ አልነበረውም። እኛ ደግሞ በዛ ወጣትነት እድሜያችን ማራቶን ውድድር የምንለው ከሐኪም ሜዳ ተነስቶ፣ በእድር ት/ቤት አድርጎ፣ ወደ ቤላ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል በመዞር በጀርመን ኤምባሲና ድልድይ በኩል አድርጎ፣ ወደ ቀበና ጉልት ዞሮ፣ የቀበናን የወንዝ ዳርቻ መንገድ ተከትሎ እዛው ሐኪም ሜዳ መግባት ነበር። አሸናፊው ፍቄንም ወላጆቻችንና የተጋበዙት እንግዶች ቆመው በጭብጨባ ይቀበሉት ነበር። እናም በእንደዚህ ባለ የወጣቶች ቀን የወጣቱ የኪነት ክፍልም ትያትርና ዘፈኖችን አዘጋጅተን ለወላጆቻችንና እንግዶቻችን እናቀርብ ነበር። የዚህንም ፕሮግራም የሚመራው አስተዋዋቂው ይኸው ፍቃዱ ሣህለድንግል ነበር። ከዚያም ዘፈኑ የሚጀመረው በአስራት አለማየሁ የጃዝ ጋጋታና ኳኳታ ነበር። መደራጀት ስንጀምር ጃዙን ከጉርድ በርሜልና ከተመረጡ ቆርቆሮዎች ነበር የምናዘጋጀው። በኋላ ግን በክራይም በልመናም ምርጥ ጃዝ ይዘን እንቀርብ ነበር። ታዲያ የአስራት ችሎታ ከፍተኛ ነበር። አሁን አሁን ሳስበው የአስራትን ክህሎት የሚደርስበት አልነበረም። እሱ ግን ያለጊዜው የተነሳ ጃዘኛ ነበር። አሁን ግን ሁሉንም እርግፍ አድርጎ ትቶታል።

ታዲያ አስራት ጃዙን ሲያንኳኳውና ሲያንኮሻኩሸው የቆነጃጅት እህቶቻችንን የዘፈን ድምጽ ከኋላው አስከትሎ እንደ እንዝርት እየተሸከረከረና እጅ እየነሳ ወደ መድረኩ የሚገባው በዘመኑ በሰፈራችን በተግባቢነቱና በመልካም ባህርዩ የታወቀው ወጣት ሰለሞን ሐድጉ (ጋንፋሬ) ነበር። ጋንፋሬ ጨዋታን ማወቅና ፍቅር ስለነበረው በሱ እንቅስቃሴ ሁሉም ወጣት ተደፋፍሮ ይገባና ይጨፍር ነበር። ጋንፋሬም የመድረኩ መሪ በመሆን ለጭፈራው ድምቀት ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው። ወላጆቻችንም ግማሹ "... ከዐይን ያውጣችሁ..."ሲለን ሌሎቹ ደግሞ"...የት ተማራችሁት?..." ይሉን ነበር። እኛም በነሱ ድጋፍ እየተበረታታን የሕብረተሰቡን ችግር ለመፍታት እንተጋ ነበር። ስለ ጋንፋሬ

# የቀበና ትዝታ

ሌሎች ብዙ ጽሁፎች ይኖራሉ ብዬ በማሰብ ብዙ ከመጻፍ ተቆጥቤአለሁ። ነገር ግን ከጀመርኩት አይቀር በማለት ሌላም ስለ ጋንፋሬ ልንገራችሁ። መቼም ጋንፋሬን ሳይሰምና ሳይመርቅ የሚያልፍ እናት በሰፈራችን አልነበረም። እናቶቻችንም ከገበያ ሲመለሱ እቃቸውን ተሸክመን ከምናደርስላቸው ወጣቶች ቀዳሚው ጋንፋሬ ነበር። ከሠፈራችንም ውጭ በኮከበ ፅባህ ት/ቤት በእስካውትነት እስከ ፓትሮል ሊደር (ኃላፊ) ሆኖ አገልግሎአል። እስካውቶች በጊዜው ከሚሰሩት ሥራ ዋናው ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ሲመጡም ሆነ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ የመንገዱን የግራ መስመር እንዲጠቀሙ ማስተማርና የዚህንም ስርዓት ማስከበር ነበር። በዚህም የተዋጣለት አስተዋጽኦ ነበረው። ተማሪውም ሆነ ሕብረተሰቡም ሰልጥኖ አንድ መስመር ይዞ ሲጓዝ የሞላ ወንዝ ይመስል ነበር። ዛሬ ዛሬ መኪናው፣ ሰዉና እንስሳው አንድ ላይ ሲተራመሱና ሲላተሙ፤ ይልቁንም ሀገራችን በትራፊክ አደጋ ከአለም አንደኛ ስትባል፣ የነጋንፋሬ ድካም የትም ፈሶ መቅረቱ ያሳዝነኛል። በት/ቤት እስካውትነትም ሆነ በቀበና አብሮ አደግነት ከጋንፋሬ ጋር ብዙ ቅርርብ ነበረን። እንደ ቤተሰብም ሆነን ኖረናል። እናቴም ከልጆቿ እሱን የምትለይበት አንጀት አልነበራትም። ወደ ጎልማሳነት እድሜ ስንደርስም እንደማንኛውም ወጣት የጃንሆይን ከስልጣን መውረድ ስንደግፍ ተከትሎ የመጣውን የወታደራዊ አገዛዝ ተቃውመናል። ምንም እንኳን አብዛኞቻችን የወታደር ልጆች ብንሆንም የወታደራዊውን መንግስት ከሚቃወሙት ጋር ሆነን ታግለናል። ታዲያ ሰለሞን ኃድን (ጋንፋሬ) በተፈጥሮው ለጥሩ ነገር ሁሉ የሚደክም ስለ ነበረ ከአብሮ አደጎቹ ጋር በመሆን በይፋም ሆነ በህቡእ በተነሳው የተቃውሞ ንቅናቄ ትልቅ ተሳትፎ ነበረው። በወጣቱ ክንፍ የራሱ የነበረ አሻራ ሊኖረው እንደሚችል እገምታለሁ። የተጀመረውም የተቃውሞ ትግል እየተጠናከረ በሄደም ጊዜ ሠፈራችን ልዩ ትኩረትና ክትትል ተደርጎበት ነበር። ትግሉ ሰላማዊነቱን ለቆ ወደ ትጥቅ ትግልም ሲገባ ሁኔታዎች ለሠፈራችን ወጣቶች እጅግ አስቸጋሪ ሆነው ነበር። በዚሁ የመረረ ትግልም ብዙዎች አብሮ አደጎቻችን ተሰውተዋል። ይህ ወቅት ሰው ከቤቱ ወጥቶ እስከሚመለስ በሃሳብ የሚናወጥበት ዘመን ነበር። አንድ ቀን ከሥራ ወደ ቤቴ ገብቼ፣ እራቴን በልቼ ከማርክስ መጽሐፍት ስለ ሶሺያሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ የሚያስረዳው ክፍል ለመረዳት አስቸግሮኝ ትቸው ለመኝታ ጋደም እንዳልኩኝ የመኝታ ቤቴ መስኮት ተንኳኳ። እኔም ደንግጬ ስከፍተው ጋንፋሬ ነበር። ላብ በላብ ሆኖ ክፉኛ ደንገጦም ነበር። እጁን ጎትቼ በመስኮት አስገባሁትና የገጠመውን በሹክሹክታ አጫወተኝ።

ጋንፋሬና የትግል ጓደኞቹ ሰው በተኛበት ሰአት የባነር ሰቀላና በአስፋልት ላይ የመፈክር ሥራ ይፈጽሙ ነበር። ትግል ስለሆነ ቀበሌውም አድፍጦ ይጠብቅ ነበር። እናም ቀበሌዎች እና እነ ጋንፋሬ ፊት ለፊት ተገናኙ። ጋንፋሬ በሰፈሩ የታወቀ ወጣት ስለነበረ ወዲያው ነበር ያወቁት። ይልቁንም ከቀበሌዎቹ አንደኛው ሁላችንንም እንደ አባት ሆነው ያሳደጉን ነበሩ። ይኸውና ያዘው የብዙነሽ ልጅ ነው እያሉ ያሳድዱት ጀመር። እሱም የኮሎኔል ሣህለማርያምን ግቢ ዘሎና አቋርጦ ጫካውን ሰንጥቆ፣ በቀን ብርሃን እንኳ አስቸጋሪውን የሠፈራችንን መንገድ በጨለማ በሩጫ አምልጦ ነበር እኔ መስኮት ላይ የደረሰው። እኛም ልንሰዋለት ለቆምንለት አላማ መጠንከር እንዳለብን ተነጋግረን፤ የእኛ ቤትም ጥሩ ምርጫ አለመሆኑን ተነጋግረን (በቀበሌው ይሰለል ስለነበር) ወደ ፊት ሊያደርግ ስለሚገባው ተመካክረን በኪሴ የነበረውን ሰጥቸው ሲነጋጋ በገባበት መስኮት ወጥቶ ሄደ። እሱ ከወጣ በኋላ ግን ፊቴ በለቅሶ ብዛት አብጦ ነበር። ሁለተኛም እንገናኛለን የሚል ግምት አልነበረኝም። ከጊዜ በኋላ አሲምባ መግባቱ ተሰማ። የትጥቅ ትግሉም ሲከሽፍ ሱዳን ካርቱም እንደ ደረሰ ተነገረ። እኔም ካርቱም በሚሰራ የሥራ ባልደረባዬ በኩል አስፈልጌ ላገኘው ሞክሬ ሳይሳካልኝ ቀረ። በዚህ ፍለጋ ሌላውን አብሮ አደጋችንን ባንኬ ኃይሌን አግኝተውት ነበር፤ እሱም ግንኙነቱን ስላልፈለገው አልቀጠልንም።

ስለ ጋንፋሬ ከዛ በኋላ የሰማሁት አሜሪካ ከገባ በኋላ ነበር። የተረፈው ሁሉንም ትቶ ወደየግል ሕይወቱ ገባ። እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1984 ዓ/ም እኔም ናይጀሪያ ሌጎስ ተመድቤ ሄድኩኝ። ከዛም እየደወልኩለት እንገናኝ ነበር። አሜሪካን ድረስ ሄጄ ላየው እንደምፈልግም ነገርኩት። እሱም ጋበዘኝ። ለጥቂት ቀናት የወጣሁት ዛሬ ነገ ሲባል ሦስት ወር ተቀመጥኩኝ። ኒዮርክን፤ አትላንቲክ ሲቲንም አስጎብኝቶኛል። ዲሲና ዙሪያውንም በባቡር እየዞርሁ እጎበኝ ነበር። እንግዲህ ተመልከቱት እግዚአብሔር ጋንፋሬን ከስንቱ መአት አውጥቶ እኔም ያላሰብኩትን አዲስ አለም አሳየኝ። ከዚያ በኋላ አሜሪካ የሄድኩት እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1988 ዓ.ም ለሦስት ወር ትምህርት ነበር። በዚህ ጊዜ እኔም ባለቤቴን ለማስጋበዝ እድል አገኘሁና ወደ አሜሪካ መጣች። የመጀመሪያ ልጃችንን ሰባተኛ ወር እርጉዝ ነበረች። እኔም እስዋ ከወለደች በኋላ ስድስት ወር ያህል ቆይቼ ተመለስኩኝ። የተውኳት ካክስተዋ ጋራ ቢሆንም ጋንፋሬንም አደራ ብየው ነበር። እሱም ከጎንዋ አልተለያትም ነበር። ከልጁ ክርስትና በኋላ ግን በቤተክርስትያን የክርስትና አባት መሆኑን ተረዳሁ። ለእኔም ከአብሮ አደግነት አልፎ አበልጃሞች ሆንን። ጋንፋሬ ለኔ ብዙ ነበር። ከርቀቱ የተነሳ ደግሞም ኑሮአችንን ለማሸነፍ በየፊናችን ስንሮጥ ግንኙነታችን እየላላ ቢሄድም፤ ግን ስለ አሜሪካ ሳስብ ጋንፈሬን ጨምሬ ነበር።

የዛሬ ዓመትም ወንድሜን ለማየት ስሄድ ሁለት ቀን ተገናኝተን ተጨዋውተን ነበር። ጋንፋሬን አለማወቅም መጎዳት ይመስለኛል። የጋንፋሬን ፍቅር ያልተቋደሰ ሰው ምን ያህል ቀርቶበት ይሆን? ሐዘኑን ቤተሰቡንና ወዳጆቹንስ ምን ያህል ጎድቶ ይሆን? የመጨረሻውን ቀን ሥረዓት ፎቶግራፍ አይቼ፣ የሸኘውን ሕዝብ ብዛት ተመልክቼ እርግጥ ጋንፋሬ ዘመናትም ያልቀየሩት ፍቅር እንደ ነበር ተረድቻለሁ።

እግዚአብሔር ምንም ክፋት የማያውቀው ወንድማችንን ነፍሱን ደጋግ አባቶቻችን ወዳረፉበት እንዲጨምርልን እንለምነዋለን! ለምትወደውና በደስታው፣ በሃዘኑና በህመሙ ለረጅም ዘመን ከጎኑ ላልተለየችው ባለቤቱ ኤልሲ፣ እንዲሁም በጣም ለሚጨነቅለት ልጆቹ፣ ሐዘኑ ከአዕምሮአቸው ለማይወጣው ቤተሰቦቹ፣ ለሚያውቁት ጓደኞቹና አብሮ አደጎቹ ሁሉ ከሐዘኑ ይጽናኑ ዘንድ እመኛለሁ።

ደመቀ ጀምበሬ



# የፎቶ አምድ



የጭውውት ጊዜ


ከቀበና ማህደር




LAS VEGAS





## እነ ማንን ያውቃሉ?















ቤት ለምቦሳ



የቀበና ጠጣር በሜሪላንድ





ቀቤዎች በፀአዳ አስመራ



የቀበና ጠጥር በሜሪላንድ


የቀበና ፍሬ ቲም













ትዊስት ወደ ግራ ትዊስት ወደ ቀኝ
እራቴን ስበላ ፍቅርሽ አነቀኝ

# ከግጥም አምባ

## ቀበናን በትዝታ እይታ (ወጣገባ) የግጥም ሥንኝ

አንቺ ሾላ፤ አንቺ ሾላ የቀበና፤ እስቲ አሁን ንገሪና
የዚያን ክፉ ጊዜ፤ የዚያን የክፉ ቀን፤ ታሪክሽ ነውና
አላየሁም፤ አልሠማሁም፤ ብለሽ እንዳትይኝ
እኔ፤ እኔው ብቻ ላንቺ፤ በቂ፤ ምስክር ነኝ።
አዎን፤ አይቻለሁ፤ አንቺም፤ በጥይት እግርሽን ተጎድተሽ
ዝምታው፤ ዝምታው ምንድነው ? አይተሽ የለም ባይንሽ?
ሰምተሽ የለም እንዴ ! መትረየሱ፤ ኡዚው ሲንጣጣብሽ
አትክጅም፤ መቼም አትክጅም፤ ካልሆነ በቀር አሁንም ፈርተሽ።
አንቺ ሾላ፤ አንቺ ሾላ የቀበና፤ ሰው አምጥተው ሲረሽኑ አጠገብሽ
በለሊቱ፤ በለሊቱ፤ በድቅድቅ ጭለማ በአመሻሽ
በዚያን ወቅት በዚያን ጊዜ፤ ኡ! ኡ! አለማለትሽ
ንገሪና ምን አስፈራሽ፤ ምንነበረ ጭንቀትሽ፤ ጉሮሮሽን የዘጋሽ??!!።
አትፍሪ፤ አትፍሪ ዛሬ አትፍሪ፤ እውነት ተናገሪ
የሰው ደም፤ አዎን የሰው፤ ደም አጠገብሽ ሠርቶ ኩሪ
አንቺ ሾላ፤ አንቺ ሾላ የቀበና፤ ለታሪክ የጎለተሽ የገተረሽ
ተናገሪ፤ ተናገሪያ ! ምንድነው ዝምታሽ??
ዝምታሽ፤ ዝምታሽ ምንድነው? ዛሬ፤ ንገሪና ?
ተመርመሪ ተጠየቂ፤ የምትነግሪን ብዙ አለና!!።
አንቺ ሾላ፤ አንቺ ሾላ፤ የቀበና፤ ዛሬ፤ ዛሬስ ወዮልሽ ፈርዶብሻል
ምስጢር አውጭ፤ ምስጢር፤ አውሪ ይሻልሻል !!
ማናቸው እነሱ ? ማናቸው? እነማን ነበሩ ?
በጥይት፤ በጥይት ሰው የሚቆሉ፤ እሚዘርሩ !!
አላየሁም፤ አልሠማሁም ብለሽ፤ ኋላ እንዳትይ
እግዚአብሄር አለ፤ ከላይ፤ እንዳትሆኚ ቃለ አባይ።
ወገኑን !፤ ወንድሙን!፤ እህቱን !፤ ጎረቤቱን
ሠይጣኖች!፤ አውሬዎች!፤ ምን እንበላቸዉ እነዚህን!!!
የሰው ደም ጠጭዎች! ፤ የሰው ደም ላሾች
የሰው ፍጡር ሣይሆኑ፤ ያበዱ፤ ልክስክስ ውሾች!!!
ወይኔ፤ ወይኔ ወይኔ፤ ቅጥል ነው እርር ነው ወይኔ!!
ምነው፤ ምነው!! ዛሬ፤ ዛሬ!! በሆነ ያኔ!!
ምን ነክቶን ነበር ጎበዝ? ምን ነበር የሆንነው ወንድሞች እህቶች?
ለዚያውም! ለዚያውም በጀግኖች ሠፈር፤ ባይበገሬዎች!!
የምን አዚም ነው? የምን ጥንቆላ? የምን መተት ?
ልጁን፤ አዎን ልጁን፤ አምሣያ ልጁን ወስዶ ፤ አጠገቡ ሲደፋው በጥይት!!
በያለበት! በየጥሻው፤ በየግቢው፤ ከቤቱ ውስጥ
በሥርቤቱ ፤ በሶስተኛ፤ በዓለም በቃኝ ሲነርተው በፍልጥ!!
ወንድሞቹ ? እህቶቹ? ምን ነበረ፤ ምክንያቱ?
ዝም ብሎ፤ አዎን! ዝምብሎ ! ከመሬት ተነስቶ በዱላ፤ በጥይት መምታቱ!!
ደርግ ይውደም! አዎን ይውደም!! መጥፋቱ ሲያንሰው ነው
የእሱ ሥራ ነው! የሱ ጅማሮ፤ ይኸን ሁሉ ጥፋት ያመጣው!!
ይቆጫል! ይቆጫል ያንገበግባል ! ምን ያደርጋል የፈሠሠ ውሃ አይታፈስ!
ባትኖር!፤ አዎን፤ አንተ ባ ት ኖ ር!!! አንተ ባትኖር! የኮሪያውስ
ጀግና የኮንጎው አንበሣ!! ይህ ሁሉ በደል ሲደርስ
የልጆቻችሁ፤ የወገናችሁ ደም በከንቱ፤ አያስችልህም ነበር እንደጎርፍ ሲፈስ!!!
ይህን ግፍ ፤ ይህን በደል ብታዩ ኖሮ!! ኖ ሮ !! በቁማችሁ
አይደርስም ነበረ!! ይህ ሁሉ ፍጅት የልጆቻችሁ የወገናችሁ!!
ተነሱ፤ ተነሱ ጀግኖች!! ጀግኖች ተነሱ!! የምን እንቅልፍ ፤ የምን መኝታ ነው!!!
ቀበና ቀበኔ! ቀበና ቀበኔ!! ቀበና ተንዶ!! እየፈረሠ ነው!!!
ቀበና፤ ቀበና፤ አዎን ቀበና ፤ የቀበና ሾላ
እባክህ ጠብቀን፤ ሁንልን ጠለላ፤ ሁንልን ከለላ።
ቀበናችን፤ ዞሮ መግቢያችን፤ መንደራችን፤ መዳሪያችን፤ መኳያችን
አለኝታችን፤ ቅርሣችን፤ ማደሪያችን፤ ማኩረፊያችን ፤
ቀበና፤ የጀግኖች ሠፈር፤ የነዚያ፤ አይበገሬዎች
ጀግኖች፤ አምራች፤ የአገር ድንበር አስከባርዎች፤
ቀበና ተወልጄ፤ ቀበና አድጌ፤ ሁሉ በጄ፤ ሁሉ በደጄ ነበረ ተረቱ
ያ ሁሉ ቀረና ተረቱ፤ በረታብን በሰው አገር መንከራተቱ።
እንደዚያ እንደጥንቱ እንደነበርን አሠባስበን
አይደለም መሰደዳችን አንተን ንቀን አንተን ጠልተን
ቀበና ቀበኔ፤ ቀበና ቀበኔ ፤ ይቅር በለን ታረቀን
አንቀርም ከቶ፤ ተመልሠን እንመጣለን።
አይ ቀበና ስምህ ትልቅ ሥራህ ብዙ አይደክምህ
ከእንጦጦ ተራራ ጀምረህ፤ ምናምን ተሸክመህ
ለኛ ጤንነት ብለህ ፤ ቆሻሻ አግተልትለህ
ማዘጋጃ የጠላውን፤ የናቀውን፤ አንተ፤ የነሱን ሥራ ትሠራለህ፤
ወይ ቀበና፤ ወይ ቀበና የአንተ ውለታ፤ አንተ ባትኖር
በኮሌራ፤ በወረርሽኝ አልቀን ነበር።
ቀበኔ ድንቅ ነው ፤ ያንተ ሥራ ተወርቶ አያልቅም
ካልነኩህ አትነካም ፤ ከነኩህ አትለቅም
ዱቤ ይመስክራ ፤ ስንቱን ሰው በልተኸው የለም።
ቀበና ቀበኔ፤ ቀበና ቀበኔ፤ እኛ ላንተ፤ አንተ ለኛ
የልጆቻችን፤ የድፍን ፍጥረት፤ መዋኛ፤ መዝናኛ።
እባክህ መርቀን ደግመህ ደጋግመህ
ባንድነት በፍቅር ኑሩልኝ ብለህ።
እኛም ደግሞ ላንተ፤ ላለብን ውለታ
በቃህ እንዲልህ እግዜር፤ ጠዋትና ማታ።
በፆምና ፀሎት እየተንበረከክን
ያለመሠልቸት ሁሌ፤ ሁሌ ፤ ምንጊዜም እንፀልይልሃያለን።
ለኛ እንዳሰብክልን አስከዛሬ ድረስ እንደተንከባከብከን
አቀበት ቁልቁለት መውጣት መውረዱን።
ይገበሃል ማረፍ በዝቶብሃል ሥራ
የምትጦርበት ቤት የምታርፍበት ሥፍራ
እግዜር እንዲሰጥህ ብለነዋል አደራ!!!

ለገሠ ዘውዴ (ከቨርጂኒያ፤ አሜሪካ)

# ስለቀበና ቃርሞሽ የግጥም ስንኝ

ዱሮ ነው ፤ጥንት ነው፤ አገር ቤት እያለሁ
አንቴ ነው፤ ማሲንቆ እየመታ ቀበና ሲል ሰማሁ
ምን ይሆን ቀበና ማለት፤ ማሰላሰል ጀመርሁ
ቀስ አልኩና ኋላ፤ መምታቱን ሲጨርስ
ምን ማለት ነው ብዬ፤ ቀበናን ጠየቀት እንዲሠጠኝ መልስ።
በስሜት ተውጦ መምታቱን ቀጠለ
ድምፁን ከፍ አድርጎ እንደዚህ እያለ፤
ቀበና ቀበኔ ቀበና ቀበኔ፤ የቆንጆዎች አገር፤
የጉብሎች መንደር እንደምነሺልኝ
እኔ በአንቺ ፍቅር አይመሽ አይነጋልኝ
የሸማ ማጠቢያው ቀበና ነው ወንዙ
አልማዝ ትመጣለች ለማጠማዘዙ።
የቀበና ነገር በልጅነት መንፈስ ሥሜቴ ተነክቶ፤ ተሳልኩለት ስለት
እባክህ አምላኬ፤ ይህ ቀበና እሚሉትን አሳየኝ ብዬ አልኩት
ስለቴ ተሳክቶ ከለታት አንድ ቀን ከዚያ መጣሁና
አመሻሽ ላይ ገባሁ ከሰሜን ቀበና
በጣም የሚገርመው ያረፍኩበት ቤት
ከወንዙ ዳርቻ የቅርብ እርቀት
በጠዋት ተነስቼ ወረድኩኝ ለማየት
ከዚያም ስመለከት የውሃውን ጥራት
በጣም !! ደስ ስላለኝ፤ ሣይጠማኝ ጠጣሁት።
እውነቴን ነው እምለው ፤ በ 1949'ኙ፤ ዓመተምረት
የቀበና ውሃ፤ ውበትና ጥራት
አይጠገብም ነበር ቢጠጡት ቢጠጡት።
ዛሬ እንዲህ ቆሽሾ ለማየት ቢያስጠላም
ሥመ ገናና ነው ቀበና ምንጊዜም
ለኛ መጠሪያችን ይኑር ለዘላለም።
እኔም ከዚያ አገር ቤት ከመጣሁ ጀምሬ
አብሬው ኖራለሁ በደም ተሳስሬ፤ በቀበኖች ፍሬ።
ያ' አንቴ ፤የዘፈናት ዘፈን፤ የቀበና ጉዳይ
ምርቃት ሆነልኝ፤ ልጆች ወልጄ እንዳይ።
የቀበና መንገድ ቀጭን ጉራንጉሩ
ዳገት ቁልቁለቱ ከዚያም ሸንተረሩ
የአጣናው ውግርግር የሰንሰል አጥሩ
ይናፍቃል እሱም ሰው አገር ሲኖሩ።
ቀበናን ያቀኑ ቤተሰቦቻችን፤ ጎረቤቶቻችን፤ በህይወት ቢኖሩ አሁን
የብረት በሩን፤ የብረት አጥሩን፤ ያዩት ነበር፤ ልዩ ውበቱን።
ግንባታው አምሮበት ፤ ከእንጨት ይልቅ፤ በሸክላ ብሎኬት
ለቀቤ ሆኖታል፤ ታላቅ፤ የውበት ድምቀት።
ይህ ያሁኑ ነገር፤ ደግሞ ይቀርና
በግዙፍ ህንፃ፤ መተካቱ ፤ አይቀሬ ነውና።
እኔ ለቀበና፤ ለ-06፤ ተወላጅ በሙሉ
በውስጥም፤ በውጭም፤ ነዋሪ፤ ለሆናችሁ ሁሉ
አደራ የምለው፤ የምማፀናችሁ
ይህ ማህበራችን፤ ይህ ማበራችሁ
ይህ ያንድነት መንፈስ፤ ይህ ህብረታችን
ዘላለም እንዲኖር፤ መተሣሠባችን መነፋፈቃችን
አደራ እላለሁኝ፤ ቃል በሠማይ በምድር
እግዜር ያፅናልን፤ ይህን ያንድነት ፍ ቅ ር ር!!!!!!

ለገሠ ዘውዴ (ከቨርጂኒያ፤ አሜሪካ)

# የቀበና አብሮ አደጎች

ወንዙና ፏፏቴው ሜዳው ሸንተረሩ
በጣም ያስደስታል ቀበና ሲኖሩ፣
የቀበና፣ የአራት ኪሎ፣ ስድስት ኪሎ፣ የምኒልክ
በኛ ጊዜ የኛ ፍቅር የለውም ልክ
ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናየው
ት/ቤት ያሳለፍነው፣ ኩኩሉ ብለን አብረን ያደግነው
በየኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር ብለን በቄስ ት/ቤት
በተምሮ ማስተማር በየቀበሌያችን የተሳተፍንበት
ዘመቻ የሄድንበት በእድገት በህብረት
በቤተመቅደስ ያደግንበት በልጅነታችን
ቀበና አብሮ አደጎች አለ ትዝታችን
ብዙ ነው ትዝታው ወደኋላ ስናይ
በፖለቲካውም ተሳትፈናል በሀገር ጉዳይ
ወላጆቻችን በስርአት ማሳደጋቸው
ፍቅር ሰጥተው አውርሰውን ማለፋቸው
እኛም ዛሬ ልጆቻችንን አስተዋውቀን
የነሱ ቅርስ እንደነበርን አገናኝተን ፣
ትዝታ አለ በሁላችን ቀበና ነው ሰፈራችን
በፍቅር ነው እድገታችን፣
ዘናጮች ነን የታወቅን በዘመኑ
ቅብጠት የለ ሁሉ ነገር በመጠኑ፤
በህይማኖት የታነፅን የነበረን የሀገር ፍቅር
ተሰብስበን እያወጋን በየቤቱ አብረን ማደር
በፖለቲካው ተሳትፈናል በዘመኑ
አሉን ወንድሞች አሉን እህቶች አሉን ጓደኞች
ተሰውተው መና የሆኑ
ቢለዩንም ዛሬ በሞት ብናጣቸው
በትዝታ ለምንጊዜም የማንረሳቸው፤
ቀበና ሰፈሩ ጎረቤቱ ይመሰክራል
እንደ አንድ ቤት አሰባሰቦ አሳድጎናል
ሠፈሩ ይደምቃል ስንወጣ ወደሜዳ
ጥምቀቱ ሲከበር ስንታይ በጃልሜዳ
የፈረንሳይ የቀበና የአቦ ልጆች
በፊትም አሁንም ቤተክርስትያን አፍቃሪዎች
በማዕረግ ያደግንበት ልጅ ወልደን ያሳደግንበት
እኛ ተድረን ልጅ የዳርንበት፤

ወላጆቻችን ልጅ ሲድሩ
ሰርግ ቢኖር በሰፈሩ
የታዘዝነውን ስንሰራ ወላጆቻችን በኛ ሲኮሩ
የከፋ ሀዘን ቢኖር የመረረ
ሁላችንም እንደ አንድ ቤት ሆነን እናዝን ነበረ
ማህበራዊ ህይወታችን በፍቅር የሰፋ
በደስታ በሀዘን እርስ በርስ አንጠፋፋ
ስድስት ኪሎ አራት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ገብተን
አንዳንዶቻችንም ጥሩ ስራ ይዘን
አብዛኛውን ጊዜያችንን በጥናት ስናጠፋ
እየተጋገዝን ነበር በትምህርት እንድንገፋ
ትዝታው በጣም በጣም በጣም ብዙ ነው የቀበና
መቼ እንዲህ ተፅፎ ተወርቶስ ያልቅና
እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ ቢገፋም ዕድሜያችን
የማይረሳ ትዝታ አለ በህይወታችን
እስከዛሬ ድረስ እየተደዋወልን እየተጠያየቅን
ችግር ቢኖር በደስታ እየተነጋገርን
የድሮን ነገር በትዝታ እየተጨዋወትን
ከልብ እየተረዳዳን እስከዛሬ እየተጠያየቅን
ይሄው ለዚህ ቀን ፈጣሪ አድርሶናል
ከልጆቻችን ከልጅ ልጆቻችን ጋር አንደገና አገናኝቶናል
እግዚአብሔር ይመስገን ለዚህ ቀን አብቅቶናል
በዚህ ፅሁፋችን ትዝታችንን ገልፀናል
ለቀሪው ህይወታችን እግዚአብሔር ይጠብቀናል
ለእሱ አደራ ሰጥተናል።
እናመሰግነዋለን ።
እግዚአብሔር ይመስገን።

ከቀበና አብሮ አደጎች ።

ሀያሉ እግዚአብሔር ቀሪ ዘመናችንን ባርኮ ለሚቀጥለው ዓመት በሰላምና በጤና ከነቤተሰቦቻችን ያድርሰን ። አሜን

መሠረት በቀለ

## ደያስ

ደያስ ጥዑሙ የምግቦች ንጉሥ
ድብልቅልቅ ያልክ አንጀት አርሥ
የደጉ ቀን ጥሪት
የጥጋብ ምልክት
የጥሩ ጊዜ ማስታወሻው
የካምፕ የቀበና መለያው
ስንቱ ቀን ገፋብህ
ችግሩን ተወጣብህ
ቤሳ ቤስቲን ሳናወጣብህ
ምንም ሳንከፍልብህ
አንዱ በጆንያ
ሌላው በማዳበርያ
በጨርቅ በአንሶላ
በተገኘው ሁሉ መላ
ቁና ቁና እየተነፈስን
ከጥቂት ጉርሻ ለማያልፈው ሆዳችን
ያገር ምግብ ተሸክመን
ከካምፕ ብቅ እንላለን
ከዚያም አረፍ ብለን
የምንችለውን ያህል አጎድጉደን
ለጓደኛ ለቤተሰብ አካፍለን
የቀረውን ቸብ እናደርገዋለን
ሳንቲሙን እንፈልገዋለን
ሌላ ሱስ ደግሞ ስላለን
ዋ! የደያስ ውለታ
ዋ! የደያስ ጨዋታ
ለሚያውቁት ብቻ ለቀመሱት
ሚስጥሩ የሚገባ፣ ለኖሩበት
ደያስ
የምግብ ንጉሥ
አንጀት አርስ።

ቆለኛው (June, 2016)

## ትናንት እና ዛሬ

ትናንት እና ዛሬ መንትዮቹ
ወንድማማች፣ እህትአማቾቹ
አንድ ሆኖ ፍጥረታቸው፣ ዘራቸው
ለየ ቅል ነው ጠባይ፣ ስራቸው
አንዱ ንፋግ
ሌላው ደግ
አንዱ ጨካኝ
ሌላው አዛኝ
ወይ የጊዜ ሚስጥር
የናት ሆድ ዥንጉርጉር
ትናንት ጨካኙ፣ ሚስጥረኛው
የዛሬን ታሪክ እያወቀው
ትንፍሽ ሳይል ሳይናገር
የዛሬን ጉዳይ ሳይዘረዝር
የዛሬን ታሪክ ደብቆ
ሚስጢር አርጎ ሸምቆ
ሳይተነፍስ፣ ሳይወጣው ቃል
ለዛሬ አሳልፎ ይሰጣል

# ከግጥም አምባ


ትናንት ቸር ቢሆን ኖሮ
ዛሬን ቢያሳየኝ መንጥሮ
ዛሬ ላይ የሚገጥመኝን
ከፊቴ የተደቀነውን
ደግና መጥፎ ሰውን
ጠላትና ወዳጄን
የቱ እንደሚጠቅም፣ የቱ እንደሚጎዳ
ማን እንደሚታመን፣ ማን እንደሚከዳ
ሆይ ሆይ ያለው፣ የሞቀው
እዩኝ እዩኝ ያለው
እንደሚከስም እድሜ እንደሌለው
በዝምታ የተያዘው በለሆሳስ
መሆኑንም ዳር የሚደርስ
ይህን ሁሉ ቢነግረኝ
በወቅቱ ቢያሳውቀኝ
ትላንት ላይ ሆኜ የዛሬን ቢያሳየኝ
ሁሉን አንጠርጥሬ፣ አበጥሬ
መንገዴን፣ ጉዞዬን አሳምሬ
እነጉድ ነበር፣ እጓዝ ነበር
ትናንት ባይጨክን ኖሮ ባያመር
እስቲ እየው ዛሬን
አባ ለጋስ ቦረቦሩን
አንድም ሳይደብቅ የሆዱን
ያሳየኛል አሁን ያለሁበትን
ዛሬ የደረስኩበትን
ሚስጥር አያውቅ መሸሸግ
ከቶ ምን ሲታሰብ፣ ምን ሲደረግ
መውደቄን ወይ መነሳቴን
መሸነፍ ወይ ማሸነፌን
አባ ደፋር ይነግረኛል
ማንን ፈርቶ ዛሬ እርጭ ይላል
ዝርግፍ አድርጎ ያሳየኛል
አረረም መረረም ደጉ ዛሬ ይሻለኛል

ቆለኛው (June, 2016)





ፎቶ ገዛኸኝ ታደሰ July, 2014



ፎቶ ገዛኸኝ ታደሰ July, 2014